# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ዓርብ

84ኛ ዓመት ቁጥር 080 ኅዳር 20 ቀን 2017 ዓ.ም ዋጋ 10:00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!




ፎቶ፡ ዳኜ አበራ

# «ብልጽግና ከጠላትና ወዳጅ የፖለቲካ ሥርዓት ወደ ሃሳብ ልዕልና የተሻገረ ፓርቲ ነው»

**- ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ተመስገን ጥሩነህ**

**ማህሌት ብዙነህ**

አዲስ አበባ፡- ብልጽግና ከጠላትና ወዳጅ የፖለቲካ ሥርዓት ወደ ሃሳብ ልዕልና እና ገንቢ የተፎካካሪ ፖለቲካ የተሻገረ ፓርቲ መሆኑን የብልጽግና ምክትል ፕሬዚዳንትና ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ ተመስገን ጥሩነህ ገለጹ።

ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ ተመስገን ጥሩነህ እንደገለጹት "የሃሳብ ልዕልና ለሁለንተናዊ ብልፅግና" በሚል መልዕክት የብልጽግና ፓርቲ አምስተኛ ዓመት የምሥረታ በዓልን አስመልክቶ የተዘጋጀውን የፎቶግራፍ አውደ ርዕይን ትናንት በሳይንስ ሙዚየም ሲከፍቱ እንዳሉት፤ ብልጽግና አካታችነትን፣ ሚዛን መጠበቅን፣ ስብራት መጠገንን እና ፍትሐዊ ተጠቃሚነትን መሠረት በማድረግ የተመሠረተ ፓርቲ ነው። አካታችነትን ለመተግበርም ጥልና ልዩነት የሚፈጥሩ ግንቦችን ማፍረሱን፣ ከጠላትና ወዳጅ

ብልጽግና ከጠላትና ወዳጅ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል



# አሳሳቢውን የሳይበር ጥቃት ተጋላጭነትን ለመቀነስ

**ወርቅነሽ ደምሰው**

**ዜና ትንታኔ**

በመላ ዓለም የሳይበር ደህንነት ስጋት እየጨመረ ይገኛል፤ ኢትዮጵያም የሳይበር ጥቃት ተጋላጭነቷ እየሰፋና እየጨመረ ስለመምጣቱ የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር መረጃ ይጠቁማል።

በኢትዮጵያ የተደረጉ የሳይበር የጥቃት ሙከራዎች አስመልክቶ የወጡ መረጃዎች እንደጠቆሙት፤ በ2008 በጀት ዓመት 214 ፣ በ2009 በጀት ዓመት 479፤ በ2010 በጀት ዓመት 576፣ ሙከራዎች ተካሂደዋል። እነዚህ የሳይበር ጥቃት ሙከራዎች በየዓመቱ እየጨመሩ ሄደው በ2014 በጀት ዓመት 8ሺህ 845 ደርሷል።

በ2015 ዓ.ም 6ሺ959 የሳይበር ጥቃት ሙከራዎች የደረሱ ሲሆን፤ በ2016 ዓ.ም ደግሞ

አሳሳቢውን የሳይበር... ወደ ገጽ 6 ዞሯል

# በጅምር የቆሙ የጤና ተቋማት እንዲጠናቀቁ የምክር ቤቱ አባላት አሳሰቡ

**ራስወርቅ ሙሉጌታ**

አዲስ አበባ፡- በሀገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች በጅምር የቆሙ የጤና ተቋማት እንዲጠናቀቁ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት አሳሰቡ። ለረዥም ዓመት ያገለገሉ የመጀመሪያ ደረጃ ሆስፒታሎች ወደ አጠቃላይ ሆስፒታልነት እንዲያድጉም ጠይቀዋል።

ምክር ቤቱ ትናንት መደበኛ ስብሰባውን ባካሄደበት ወቅት፣ አባላቱ ለጤና ሚኒስትር ባቀረቡት ጥያቄ ፤ በርካታ ከፍተኛ የጤና ተቋማት በጅምር ቆመዋል። በዚህም የተነሳ በርካታ ዜጎች

በጅምር የቆሙ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል

# አየር ኃይሉ «ጸሐይ 2» የተሰኘች አውሮፕላን ለበረራ ብቁ አደረገ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ አየር ኃይል "ጻሐይ 2" የተሰኘችና በአየር ኃይሉ የተሠራች አውሮፕላን ለበረራ ብቁ ማድረጉን ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ገለፁ።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ በማህበራዊ ትስስር ገጻቸው ባስተላለፉት መልዕክት፤ በጸጥታና ደህንነት ተቋማት ያከናወነው የሪፎርም ሥራ ኢትዮጵያን የሚመጥንና ዘመን ተሻጋሪ ተቋማትን ለመገንባት ጠንካራ መሠረት የጣለ ነው ።የኢትዮጵያ አየር ኃይል ደግሞ በዚህ ረገድ ተጠቃሽ ነው ብለዋል።

አየር ኃይሉ 89ኛ ዓመት የምሥረታ በዓሉን እያከበረ ባለበት በዚህ ወቅት "ጻሐይ 2" የተሰኘችና በአየር ኃይሉ የተሠራች አውሮፕላን ለበረራ ብቁ ማድረጉን ጠቅላይ ሚኒስትሩ ገልፀዋል።



አውሮፕላኗ ግዳጅን በብቃት መፈጸም የሚያስችል ቴክኖሎጂ የታጠቀች መሆኗንም ጠቁመው፤ ይህም አየር ኃይሉ በ2030 በአፍሪካ ስመጥር አየር ኃይል ለመሆን የያዘውን ራዕይ እውን ለማድረግ በትክክለኛ ጎዳና ላይ መሆኑን የሚያመላክት ነው ሲሉ ተናግረዋል።




# በአማራ ክልል በመኸር ከለማው 48 በመቶ ያህል የደረሰ ሰብል ተሰበሰበ

**ዓለማየሁ ግዛው**



አዲስ አበባ፡- በአማራ ክልል በመኸር ወቅት በሰብል ከተሸፈነው ውስጥ 48 በመቶ ያህል የደረሰ ሰብል መሰብሰቡን የአማራ ክልል ግብርና ቢሮ ገለጸ።

የአማራ ክልል ሰብል ልማት ጥበቃ ዳይሬክተር ዶክተር ማንደፍሮ አስናቀ እንደገለጹት፣ በክልሉ በመኸር ወቅት በሰብል ከተሸፈነው አምስት ነጥብ ሶስት ሚሊዮን ሄክታር መሬት ውስጥ ሁለት ነጥብ አምስት ሚሊዮን ሄክታሩን መሰብሰብ ተችሏል።

ይህም በመኸር ወቅት በምርት ከተሸፈነው ውስጥ 48 በመቶ ያህል መሆኑን አስረድተዋል።

አርሶ አደሩ አሁን ያለውን ምርት በአግባቡ እንዲሰበሰብ የተለያዩ ዘዴዎችን መጠቀም እንደተቻለ የተናገሩት ዳይሬክተሩ፤ በቀጣይም የደረሱ ሰብሎችን የመሰብሰብ ስራው ተጠናክሮ ይቀጥላል ብለዋል።

እንደ ማንደፍሮ (ዶ/ር) ገለፃ ፤ምርት በሚታጨድበት፣ በሚጓጓዝበት፣ በሚከመርበት፣ በሚወቃበት እና ጎተራ በሚገባበት ወቅት 27 በመቶ ያህል ብክነት ስለሚኖር አሰባሰቡ ከፍተኛ የሆነ ጥንቃቄንና ትኩረት ያስፈልጋል።ለዚህም አርሶ አደሩ ምርቶቹን በአግባቡ እንዲሰበስብ በግብርና አደረጃጀትና የተለያዩ የመገናኛ ዘዴዎች አማካኝነት የማስገንዘብ፣ የማስተማርና ሙያዊ ድጋፍ የመስጠት ስራ እየተከናወነ ነው።

እስካሁን ባለው ምርት የመሰብሰብ ሂደት ውጤታማ ሲሆን እንደ ገብስ፣ ስንዴ፣ ጤፍ፣ አኩሪ አተር፣ ሰሊጥና ሩዝ የመሳሰሉ ሰብሎች እየተሰበሰቡ ይገኛል ያሉት ዳይሬክተሩ፤ ዝናብ አልፎ አልፎ የሚጥል ቢሆንም ለሰብል ስብሰባው የሚያሰጋ እንዳልሆነም አመልክተዋል።

ከሚሰበሰበው የመኸር ሰብል 169 ሚሊዮን ኩንታል ምርት እንደሚጠበቅም ማንደፍሮ (ዶ/ር) ጠቁመዋል።

# በኢፕድ ሥልጠና ማዕከል የተሰጠን ሥልጠና ተግባራዊና መፍትሔ አመላካች ነው ሲሉ ሠልጣኞች ገለጹ

**ሳሙኤል ወንደሰን**



አዲስ አበባ፡- በኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ሥልጠና ማዕከል የተሠጠን ሥልጠና ተግባራዊና መፍትሔ አመላካች ነው ሲሉ ሠልጣኞች ገለጹ።

የኢፕድ በሥልጠና ማዕከሉ በፎቶ እና ቪዲዮ ኤዲቲንግ እንዲሁም በዲዛይንና ሌይአውት ለስምንት ተቋማት የሚዲያና የኮሙኒኬሽን ባለሙያዎች ሲሰጥ የነበረው ሥልጠና ትናንት ተጠናቋል። ለሠልጣኞች የምስክር ወረቅትም ተሠጥቷል።

የአዲስ አበባ ህብረት ሥራ ኮሚሽን የሕዝብ ግንኙነት ባለሙያና ሠልጣኝ አይዳ ኃይለማርያም በወቅቱ እንደገለጹት፤ ሥልጠናው ለ12 ቀናት የተሰጠ መሆኑን ገልጸው ፤በዚህም በርካታ እውቀቶችን አግኝተናል ብለዋል። ሥልጠናውም ግልጽና ተግባራዊ ክህሎትን መሠረት ያደረገ መሆኑ ይበልጥ አስተማሪ አድርጎታል ነው ያሉት።

አሠልጣኞች ሙያውን በተግባር ጠልቀው የሚያውቁና ሳይሰለቹ የማስተማር ክህሎትን የተላበሱ ናቸው። ከንድፈ ሃሳብ ትምህርት ጎን ለጎን ተግባር ተኮር ሥልጠና ሰጥተውናል። ይህም በዩኒቨርሲቲ የወሰድናቸውን ትምህርቶች እንድናስታውስ አድርጎናል ብለዋል።

ሥልጠናው ባለንበት የሥራ ዘርፍ እንዴት መሥራትና ተግባራዊ ማድረግ እንዳለብን እና የሚያጋጥሙ ችግሮች መፍታት የሚያስችል ነው። ይህም መፍትሄ አመላካች ነው ያሉት አይዳ፤ ሥልጠናው ለአጭር ቀን የተሰጠ ነው። በቀጣይ ሊራዘም እንደሚገባ ተናግረዋል።

የአዲስ አበባ ጽዳት አስተዳደር ኤጀንሲ የሕዝብ ግንኙነት ባለሙያ ወይንሸት በየነ በበኩላቸው፤ ሥልጠናው ውጤታማና ጥሩ መሆኑን ገልጸው፤ በሥልጠናው ያገኙትን እውቀትና ክህሎት በሥራቸው ላይ ተግባራዊ ለማድረግ ዝግጁ መሆናቸውን ገልጸዋል።

ኢፕድ ለተቋማት ይህ ሥልጠና አስፈላጊ መሆኑ ተገንዝቦ ሥልጠናውን በማዘጋጀቱ አመስግነው አሠልጣኞችና አስተባባሪዎች እኛን ለማብቃት በቅርበት ሲከታተሉን እና ድጋፍ አድርገውልናል ነው ያሉት።

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ምክትል ዋና ሥራ አስፈፃሚ አቶ ፍቃዱ ከተማ በወቅቱ እንደገለጹት፤ ኢፕድ ለ83 ዓመታት እለታዊ ሁነቶችን በመዘገብ ታሪክን እየሰነደ ያለ አንጋፋ ተቋም ነው። በዚህም በኢትዮጵያ የሚዲያ ታሪክ ውስጥ በቀዳሚነት የሚነሳ ተቋም ነው።

ከዚህም ባሻገር በሥነ ጽሁፍ ታሪክ ውስጥ ታላላቅ ደራሲዎችን ያፈራ መሆኑን አውስተው፤ በዚህም ለኢትዮጵያ ሥነ ጽሁፍ የበኩሉን አስተዋጽኦ አበርክቷል። ተቋሙ ለዓመታት ያካበተውን እውቀትና ልምድ ለሌሎች ተቋማት ለማጋራት የሥልጠና ማዕከል ከፍቶ ከ100 በላይ ተቋማትን አሠልጥኗል ብለዋል።

ይህንን አበርክቶውን ለማሳደግ በሚዲያው ዘርፍ የልህቀት ማዕከል ለመሆን እየሠራ መሆኑን ተናግረው፤ ዘመን የሚዋጁ ሥልጠናዎች ላይ ትኩረት መደረጉን ገልጸዋል። በተቋሙ ሥልጠና ማዕከል የተግባር ሥልጠና የወሰዱ ባለሙያዎችም የተሰጣቸውን ሥልጠና በሥራ ቦታቸው ተግባራዊ ሊያደርጉ እንደሚገባም ተናግረዋል።

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት የሥልጠናና አቅም ግንባታ ዳይሬክተር አቶ እንግዳ መኮንን በበኩላቸው፤ ኢፕድ በሥልጠና ማዕከሉ 46 የሚሆኑ አጫጭር ሥልጠናዎችን አዘጋጅቶ የተለያዩ ተቋማት አመራሮችን እና ባለሙያዎችን አሠልጥኗል ብለዋል።

አጫጭር ሥልጠናዎች የራሳቸው የሆነ ጠንካራና ደካማ ጎኖች አሏቸው። ጠንካራ ጎናቸው በሥራ ላይ የሚያጋጥሙ ችግሮችን ለመፍታት የሚያስችል ክህሎትን ያላብሳሉ። ከዚህ አኳያም ሠልጣኞች ከሥልጠናው የተገኙ ፍሬያማ ትምህርቶችን በሥራ ቦታቸው ተግባራዊ ማድረግ እንዳለባቸው አሳስበዋል።

ኢፕድ በሥልጠና ማዕከሉ የሚሰጣቸው ፕሮግራሞች ጥናት ላይ ተመሥርተው የተዘጋጁ ናቸው። በተለይ በሚዲያ አገልግሎት ውስጥ ቪዲዮ ኤዲቲንግ፣ ሌይአውትና ዲዛይን እንዲሁም የፎቶ ጋዜጠኝነት ጋር ተያይዞ የሚታዩ ክፍተቶችን በጥናት ተለይተው በሥልጠና እንዲሰጡ ተደርጓል ነው ያሉት።

ኢፕድ በሥልጠና ማዕከሉ የቴክኒክና የጽሑፍ ሥልጠና፣ ተቋማዊ ክህሎትና አሠራርን የሚያሳድጉ እና ሌሎች ሥልጠናዎችን እንደሚሠጥም ጠቁመዋል።

# ባንኩ ከኢትዮጵያ ጋር በትብብር ለመሥራት ፍላጎት እንዳለው አስታወቀ

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- የእስያ የመሠረተ ልማት ኢንቨስትመንት ባንክ ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋር በትብብር ለመሥራት ፍላጎት እንዳለው አስታወቀ።

የገንዘብ ሚኒስትሩ አቶ አህመድ ሽዴ ከእስያ መሠረተ ልማት ኢንቨስትመንት ባንክ ፕሬዚዳንት ጂን ሊኩን ጋር በኢትዮጵያ የመሠረተ ልማት ሥራዎች በሚጠናከሩበት ሁኔታዎች ላይ ትናንት ተወያይተዋል።

የባንኩ ፕሬዚዳንት ጂን ሊኩን በወቅቱ ፤ ባንኩ ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋር በትብብር ለመሥራት ፍላጎት እንዳለው ገልጸው፤ በመሠረተ ልማትን ለማሳደግ እና የአየር ንብረት ለውጥ ተጽዕኖችን መከላከል በሚቻልባቸው መንገዱች ላይ የፋይናንስ ድጋፍ ሊኖር እንደሚችል ጠቁመዋል።

በእነዚህ ጉዳዮች ላይ ከገንዘብ ሚኒስትሩ አቶ አህመድ ሽዴ ጋር መግባባቶች እንደተፈጠሩ ገልጸው፤ ተቋማቸው ኢትዮጵያ የምታከናውናቸውን የተለያዩ የልማት ሥራዎች ለመደገፍ ቁርጠኛ መሆኑን ተናግረዋል። ለዚሁ ውጤታማነትም ከሌሎች አጋር የፋይናንስ ተቋማት ጋር እንደሚሠሩ ገልፀዋል።

የገንዘብ ሚኒስትሩ አቶ አህመድ ሽዴ በበኩላቸው፤ የገንዘብ ሚኒስቴር እና የእስያ መሠረተ ልማት ኢንቨስትመንት ባንክ በጋራ ለመሥራት መግባባት ላይ ደርሰዋል ብለዋል።

የረጅም ጊዜ የእድገት ፕሮግራም፣ በሀገር በቀል የኢኮኖሚ ሪፎርምና ሌሎችንም ተግባራት ኢትዮጵያ እያከናወነች መሆኑን ለባንኩ አመራሮች አስረድተናል ያሉት አቶ አህመድ፤ ኢትዮጵያ ለምትገነባው አዲስ የአውሮፕላን ማረፊያ ከሌሎች አጋር ድርጅቶች ጋር ሆነው የፋይናንስ ድጋፍ እንዲያደርጉ ተወያይተናል ነው ያሉት።

ባንኩ መሠረተ ልማቶችን ፋይናንስ የሚያደርግ ግዙፍ ዓለም አቀፍ ተቋም መሆኑን ጠቁመው፤ ተቋሙ ኢትዮጵያ በምታከናውናቸው የመሠረተ ልማት ሥራዎች እንዲሳተፍ ተወያይተናል። በተጨማሪም የታዳሽ ኃይል ምንጭ የልማት እንቅስቃሴ ላይ የፋይናንስ ድጋፍ እንዲያደርጉ መግባባታቸውንም ጠቁመዋል።

ከባንኩ ፕሬዚዳንት ጋር የተደረገው ውይይት ውጤታማ መሆኑንም ገልጸዋል። ኢትዮጵያ በርካታ ሳቢ የኢንቨስትመንት አማራጮች እንዳሏት የገለፁት አቶ አህመድ ሽዴ፤ ሁሉም የኢኮኖሚ ዘርፎች ለሀገራዊ እድገት የበኩላቸውን ሚና እንዲወጡ የግሉን ዘርፍ ማሳደግ ይገባል። ለዚህም በርካታ ሥራዎች እየተሠሩ መሆኑን ተናግረዋል።

# “በአገልግሎቱ ያልተወራረደ ውዝፍ ተሰብሳቢና ተከፋይ ሂሳብ በየጊዜው እየጨመረ መጥቷል”

- *-የመንግሥት ወጪ አስተዳደርና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ*

# “በተቋሙ ያሉ የአሠራር ክፍተቶች ላይ የእርምት ርምጃ ይወሰዳል”

- *-የኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት*

**ዳግማዊት አበበ**

አዲስ አበባ፡- በኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት ያልተወራረደ ውዝፍ ተሰብሳቢና ተከፋይ ሂሳብ በየጊዜው እየጨመረ መምጣቱን የመንግሥት ወጪ አስተዳደርና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ገለጸ። አገልግሎቱ በበኩሉ በተቋሙ ያሉ የአሠራር ክፍተቶች የእርምት ርምጃ እንደሚወስድ አስታውቋል።

በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የመንግሥት ወጪ አስተዳደር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት የ2015 በጀት ዓመት የፋይናንስ ኦዲት ሕጋዊነትን ገምግሟል።

ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ የሺመቤት ደምሴ (ዶ/ር) በግምገማው ወቅት እንደገለጹት፤ በአገልግሎቱ በ2015 በጀት ዓመት ከአምስት ነጥብ ዘጠኝ ሚሊዮን ብር በላይ ያልተወራረደ ውዝፍ ተሰብሳቢ ሂሳብ እንዳለ በኦዲት ተገኝቷል። ከዚህ ውስጥም ከአንድ ነጥብ ስድስት ሚሊዮን ብሩ ላይ የፍርድ ቤት ውሳኔ ቢያገኝም አገልግሎቱ ክትትል ባለማድረጉ ገንዘቡ ሳይሰበሰብ ቀርቷል ብለዋል።

ሰብሳቢዋ፤ ከገንዘብ ሚኒስቴር በተገኘ መረጃም መሠረትም በ2015 በጀት ዓመት ብቻ ሳይሆን አሁን ላይ በአገልግሎቱ ያልተወራደ ውዝፍ የተሰብሳቢና ተከፋይ ሂሳብ በየጊዜው እየጨመረ መጥቷል። ይህም የአገልግሎቱ የአሠራር ሂደት ልክ እንዳልሆነ የሚያሳይ በመሆኑ በተሰብሳቢና ተከፋይ ገንዘብ ላይ ያለውን የአሠራር ክፍተት ሊፈትሽ እንደሚገባ አሳስበዋል።

አገልግሎቱ በፍርድ ቤት ማስረጃ ያገኙም ሆነ ያላገኙ ተሰብሳቢ ሂሳቦችን በአስቸኳይ የእርምት ርምጃ መውሰድ እንደሚኖርበት ገልጸዋል።

በሌላ በኩል በአገልግሎቱ ያሉ ማስረጃ የሌላቸው በርካታ የፋይናንስ ተሰብሳቢ ሂሳቦች እንዳሉ ገልጸው፤ በቀጣይ ሁሉም ሂሳቦች ማስረጃ እንዲኖራቸው በማድረግ ሪፖርት ሊቀርብ ይገባል ሲሉ አሳስበዋል።

ከገንዘብ ሚኒስቴር ወይዘሮ አባይነሽ ተሾመ በሰጡት አስተያየት፤ አገልግሎቱ በተሰብሳቢ ሂሳብ ላይ ያለው አሠራሩን ትኩረት ሊሰጠው ይገባል። እስከ መጋቢት 2016 ዓ.ም ድረስ በአገልግሎቱ ያለው የተሰብሳቢ ሂሳብ 156 ሚሊዮን 015 ሺህ 864 ብር እንዲሁም ተከፋይ ሂሳብ ከ33 ሚሊዮን ብር በላይ ደርሷል። ይህም የሚያሳየው በአገልግሎቱ የተሰብሳቢና ተከፋይ ሂሳብ እየጨመረ እንጂ እየቀነሰ አለመምጣቱን ነው ብለዋል።

የፌዴራል ዋና ኦዲተር ወይዘሮ መሰረት ዳምጤ በበኩላቸው፤ ተቋሙ ለብልሹ አሠራሮች ተጋላጭ እንዳይሆን ከተፈለገ ለተቋሙ የሥራ ኃላፊዎች እና ሠራተኞች የሚያገለግል የሥነ-ምግባር መመሪያ ሊዘጋጅ ይገባዋል ብለዋል።

በተቋሙ የሚፈጸም የትኛውም ግዥ የመንግሥትን የግዥ ሥርዓት መከተል እንዳለበትም ዋና ኦዲተሯ አሳስበው፤ የኦዲት ግኝቶቹን ማረም የሚያስችል አሠራር መዘርጋትና አሁን ተግባራዊ የሆኑ የሪፎርም ሥራዎች ተጠናክረው መቀጠል እንደሚኖርባቸው ገልጸዋል።

ኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት ምክትል ዳይሬክተር አቶ ጎሳ ደምሴ በሰጡት ምላሽ፤ በኦዲት የተገኙት የተቋሙ የአሠራር ክፍተቶች ስህተት ናቸው። በዚህም እያንዱ የኦዲት ግኝት የእርምት ርምጃ የሚወሰድበት ይሆናል ነው ያሉት።

አሁን ላይ በአገልግሎቱ ሥራ ላይ ያለው አመራርና ዳይሬክተሮች አዲስ መሆናቸውን ያነሱት ምክትል ዳይሬክተሩ፤ አንዳንዶቹ የኦዲት ግኝቶች ቀድሞ ባሉ አመራሮች ቸልተኝነትና ሕግን አለማክበርና አንዳንዶቹ ደግሞ በመረጃ መዛባት የተከሰቱ መሆናቸውን አስረድተዋል።

ከኢ-ቪዛን በተመለከተ የኦዲት ግኝት ሆኖ ሊቀርብ የቻለው በአይ ሲቲ ክፍሉና በፋይናንስ ክፍሉ መካከል ባለ የመረጃ እጥረት ምክንያት ነው ያሉት ምክትል ዳይሬክተሩ፤ በአሁኑ ወቅት ግን ይህ የቴክኒክ ችግር ሙሉ በሙሉ መፈታቱን ገልጸዋል።

አቶ ጎሳ፤ የአገልግሎቱ የተቋም ግንባታ ባልተከተለ መንገድ የተገነባ በመሆኑ በተቋሙ ያለው የአሠራር ክፍተቶች በርካታ ናቸው። በመሆኑም አሁን ላይ 11 የሪፎርም አጀንዳዎችን በማዘጋጀት አገልግሎቱ ጥራት ያለው አገልግሎት እንዲሰጥ ለማድረግ እየተሠራ ነው ብለዋል።

የሰው ሃይል አቅምን ማሳደግ፣ ሀብት ማመንጨትና ማስተዳደር በሪፎርሙ ትኩረት ተሰጥቷቸው የሚሠሩ ጉዳዮች መሆናቸውን ገልጸዋል።



አቶ ሚሊዮን ማቲዎስ

# ከወርቅ ለተገኘው የውጭ ምንዛሬ እድገት ማሻሻያው ዋናውን ድርሻ ይይዛል

**ራስወርቅ ሙሉጌታ**

አዲስ አበባ፡- በ2017 በጀት ዓመት የመጀመሪያው ሩብ ዓመት በወርቅ ማዕድን ለተመዘገበው ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ እድገት የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያው ዋናውን ድርሻ እንደሚይዝ የማዕድን ሚኒስትር ገለጹ።

ሚኒስትር ዴኤታው አቶ ሚሊዮን ማቲዎስ በተለይ ለአዲስ ዘመን ጋዜጣ እንደተናገሩት፤ በ2017 በጀት ዓመት የመጀመሪያው ሩብ ዓመት ከወርቅ ንግድ ከየትኛውም ጊዜ በላይ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ እድገት የተመዘገበበት ሆኗል። ለዚህ ደግሞ የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ ዋናውን ድርሻ ይወስዳል። የማክሮ ኢኮኖሚው ማሻሻያ እንደሌሎች ዘርፎች ሁሉ በማአድን ዘርፍ በተለይም በወርቅ ምርትና ሽያጭ ላይ በተጨባጭ የሚታይ ውጤት ለማስመዝገብ አስችሏል።

መንግሥት የዘርፉን ውጤታማነት ለማረጋገጥ የማእድን ምክር ቤት በማደራጀት በየወሩ የድጋፍና ክትትል በማድረግ ላይ እንደሆነም ጠቁመው፤ የፖሊሲ ማሻሻያው እንደተጠበቀ ሆኖ ወርቅ ወደ ብሄራዊ ባንክ ለሚያስገቡ ተጨማሪ ማትጊያ መደረጉም ለተገኘው ውጤት እገዛ አድርጓል።

እንደ ሚኒስትር ዴኤታው ገለጻ፤ ማትጊያው ወርቅ አምራቾች ለብሄራዊ ባንክ ባቀረቡት የወርቅ መጠን ላይ ተመስርቶ የሚሰጡ የተለያዩ ጥቅማ ጥቅሞችን የያዘ በመመሪያ የተደገፈ ነው።

መመሪያው አምራቹ በየትኛውም የሀገሪቱ አካባቢ ተንቀሳቅሶ ወርቁን ከሚሸጥበት የተሻለ ገቢ የሚያስገኝለት መሆኑን ገልጸው፤ በዚህም በኮንትሮባንድ ይወጣ የነበረውን ወርቅ በብሄራዊ ባንክ በኩል እንዲያልፍ አስችሏል። ቀደም ሲል በጥቁር ገበያ በኩል ይንቀሳቀስ የነበረው እና በብሄራዊ ባንክ በኩል ያለው የውጭ ምንዛሬ ተመን ልዩነት የሚያጠብ ሆኗል ነው ያሉት።

በኮንትሮባንድ የሚወጣውን በማስቀረት በሀገሪቱ ያለውን ወርቅ በአግባቡ ለመቆጣጠርና ለማስተዳደር የሚያስችል ሥርዓት መዘረጋቱን ጠቁመው፤ ይህም እንደ ሀገር ይባክን የነበረውን የወርቅ ምርት ለመታደግ ብሎም ጥቂት ግለሰቦች ብቻ ያገኙት የነበረውን ያልተገባ ጥቅም በማስቀረት ሀገር እንድትጠቀም ያደርጋል። በሕግ አግባብ ብቻ የሚንቀሳቀሱትንም የበለጠ ተጠቃሚ የሚያደርግም እንደሆነ አብራርተዋል።

ይህ አበረታች ውጤት በሌሎች ማዕድናትም ላይ እንዲደገም የማምረትም ሆነ የግብይት ሥርዓቱን ለማሻሻል ከክልሎችና ከኢንቨስተሮች ጋር ለመሥራት ጥረት እየተደረገ እንደሚገኝ አመልክተው፤ አጠቃላይ የማዕድን ዘርፉ ላይ እየተገኘ ያለውን ለውጥ ለማስፋፋትና ለማስቀጠል እየተሠራ ይገኛል ብለዋል።

ኢትዮጵያ በአለም ላይ በከፍተኛ ዋጋ ወርቅ ከሚገዛባቸው ሀገራት መካከል አንዷ ናት። ወርቅ በዓለም ገበያ ላይ የሚሸጥ አስተማማኝ የዓለም መገበያያ ገንዘብ ሲሆን በየወቅቱ እየጨመረ የሚሄድ ነው ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው ፤ በዓለም ላይ ያለው የገበያ ሁኔታ ተለዋዋጭና ተገማች በማይሆንባቸው ጊዜያት ሀገራት ያንን ወርቅ ወደመያዝ ያዘነብላሉ። አሁንም በዓለም ተገማች የማይሆኑ ሁኔታዎች ስላሉ ሀገራት ወርቅን ወደመያዝ እየተሸጋገሩ እንደሚገኙ ገልጸዋል።

በኢትዮጵያ የተረጋጋ ኢኮኖሚ እንዲፈጠር እየተተገበረ ያለው የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ ተገማች ኢኮኖሚ እንዲኖር እንደሚያስችል አመልክተው፤ ይህም በዘርፉ ለመሳተፍ ወደ ሀገር ለሚገቡ አልሚዎች ምቹ ሁኔታ የሚፈጥር በመሆኑ የተገኘውን ውጤት ዘላቂ ለማድረግ ይረዳል ብለዋል።

# በደን ልማት ዘርፍ ለ35 ሺህ ዜጎች የሥራ ዕድል ተፈጠረ

**ሰሳማዊት ውቤ**

አዲስ አበባ፡- 2017 በጀት ዓመት የመጀመርያው ሩብ ዓመት በደን ልማት ዘርፍ ከ35 ሺህ በላይ ለሚሆኑ ዜጎች የሥራ ዕድል መፈጠሩን የኢትዮጵያ ደን ልማት አስታወቀ።

የኢትዮጵያ ደን ልማት የደን ውጤቶች ንግድ ማብቃት ሙያ ብቃት ማረጋገጫ ዴስክ ባለሙያ አቶ ዘሪሁን ላቀው ለአዲስ ዘመን ጋዜጣ እንዳስታወቁት፤በያዝነው በጀት ዓመት በመጀመሪያው ሩብ ዓመት በደን ሀብት ልማት ዘርፍ 30 ሺህ ዜጎች የሥራ ዕድል ለመፍጠር ታቅዶ ለ35 ሺህ 205 ዜጎች የሥራ ዕድል መፍጠር ተችሏል።

የስራ ዕድል ከተፈጠረባቸው የስራ መስኮች መካከልም በእንጨት ማቀነባበሪያ ኢንተርፕራይዞች፣ የደን ውጤቶችን በማቅረብ፣ በችግኝ ተከላ፣በደን እንክብካቤና ጥበቃ እንደሚገኙበት ጠቅሰው፤ በደን ሀብት ልማት የሥራ ዕድል ከተፈጠረላቸው ዜጎች መካከልም 27 ሺህ 179 ወንዶች ሲሆኑ 8 ሺህ 026 ደግሞ ሴቶች መሆናቸውን አመልክተዋል።

በደን ሀብት ልማት ዘርፍ በመጀመርያው ሩብ ዓመት የስራ ዕድል ለመፍጠር ከታቀደው በላይ መፍጠር የተቻለው በደን ልማት ዘርፍ በተፈጠረው ምቹ ሁኔታ መሆኑን የጠቆሙት ባለሙያው ፤ የደን ሀብቱን በማልማትና በመጠበቅ ዜጎች በስፋት እንዲሳተፉ በማድረግ፤ስለጠቀሜታው ግንዛቤ በመፍጠር እና በዘርፉ ሰፊ የሥራ ዕድል ለመፍጠር ትኩረት ተሰጥቶ በመሰራቱ እንደሆነ አብራርተዋል።

በ2010 ዓ.ም የወጣው የደን አዋጅ 2010 /1065 ባለቤትነትን የግለሰብ፤ የማህበራት፤ የማህበረሰብና የመንግስት ብሎ ወደ አራት ከፍ ማድረጉን ያስታወሱት ባለሙያው ፤ይሄም ግለሰቦችና ማህበራት በደን ልማቱ በመሳተፍ ከዘርፉ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማስቻሉን



ገልፀዋል።

የደን አዋጅን ለማስፈፀም የወጣው ደንብም ህጋዊነት ላይ ለነበረው የአሰራር ክፍተት ምላሽ በመስጠቱና የማህበራትና የመንግስት ደን እንዴት እንጠቀማለን፤እንዴት እናለማለን ፤ምን ምቹ ሁኔታዎች አሉ የሚለውን በዝርዝር በማስቀመጡ የሥራ ዕድሉን ለመፍጠር ምቹ ሁኔታ መሆኑን አመልክተዋል።

የደን ዘርፍ የአየር ንብረት ለውጥ የሚያደርሰውን አሉታዊ ተፅዕኖ ለመቋቋም ከፍተኛ ፋይዳ እንዳለው ጠቁመው፤ ይኸው ዘርፍ አሁን አሁን በስራ ዕድል ፈጠራም ከፍተኛ ድርሻ እያበረከተ እንደሚገኝ ነው የተናገሩት።

# ርዕሰ አንቀፅ

## የለውጡ ጉዞ የኢትዮጵያን ሁለንተናዊ ብልጽግና እያቃረበ ነው!

በሀገራችን ስር ነቀል በሚባል መልኩ ለውጥ ማየትና ለውጡን ማጣጣም ከጀመርን እነሆ አምስት ዓመታት ሆነን። በእነዚህ የአምስት ዓመታት ቆይታ የታዩት የለውጥ ፍሬዎች ረጅም ዓመታትን ባሳለፍንባቸው ዘመናት ያልታዩና ይሆናሉ ተብለው የማይጠበቁ አስደናቂ ክስተቶች ናቸው። በሀገራችን ትልቅ ተግዳሮት ሆነው ይነሱ የነበሩ የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ፤ የመደራጀትና ሃሳብን በነጻነት የመግለጽ መብት ፤ ኢፍትሃዊነት፣ የኋላ ቀርነት አስተሳሰብ፣ የምግብ ዋስትና ችግር፣ የኢኮኖሚ ስብራት የመሳሰሉት ኢትዮጵያ ትከሻዋ እስኪጎብጥ ተሸክማ የኖረቻቸው ችግሮቿ ነበሩ።

እነዚህ ዛሬ ከትከሻዋ የወረዱ፣ አሁንም ጨርሰው ያልወረዱ የኢትዮጵያውያን ችግሮች ከዓመታት በፊት በሀገራችን ለውጥ እንዲመጣ ገፊ ምክንያቶች ነበሩ። ለውጡን አቀጣጥሎ ወደፊት የተራመደው መንግሥትም በእያንዳንዱ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ዙሪያ ጥልቅ ጥናት በማድረግና ችግሮችን ከመሠረታቸው በመለየት ዘላቂ መፍትሄ በሚሰጥና ሀገሪቱን ወደ ብልጽግና ማማ ሊያወጣ በሚያስችል መልኩ ሰፊ እንቅስቃሴ አድርጓል። ሀገሪቷን እግር ከወርች ጠፍረው አላሰራ ያሉ ኢ-ዲሞክራሲያዊ አዋጆች፣ ሕጎችና ደንቦችን ጨምሮ በአፈፃፀም የሚታዩ ግድፈቶችን ሁሉ ባገናዘበ መልኩ በርካታ የማስተካከል ርምጃዎች ተወስደዋል። በሪፎርም ህሳቤ አዳዲስ አሠራሮች የመዘርጋትና አሻጋሪ አስተሳሰቦችን የማመንጨትና የማስረጽ ሥራዎች ተሠርተዋል ። በዚህም ዜጋው ብቻም ሳይሆን ዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ጭምር በሚረዳው መልኩ ለውጡን ተጨባጭ ማድረግ ተችሏል። በአሁኑ ወቅት ሁሉም ዜጋ የአምስት ዓመቱን የለውጥ ፍሬዎች አይቶ እያደነቀ ፤ ቀምሶ እያጣጠመ እና እየኖረው ይገኛል።

ለኢትዮጵያ ዘመናዊ የፖለቲካ ታሪካችን ሕዝብ ፖለቲካን በሩቁ ብሎ እሳትን እንደሚፈራ ህጻን ፖለቲካን ፈርቶና ርቆ እንዲኖር ያስገደዱ ነበሩ። እርስ በእርስ ከመቀራረብ ይልቅ ጥላቻንና ቅራኔን አስፋፍተዋል። ይሄ የጥላቻና ያለመተማመን የፖለቲካ ሴራ ዛሬም ድረስ ነጸብራቁ አልጠፋም። ይሄን አካሄድ የማደስና የማረቅ ጥረት በለውጡ መንግሥት ተደርጓል። በትጥቅ ትግል ጎራ ለይተው ለሀገር ጭምር ስጋት የነበሩ የፖለቲካ ፓርቲዎች ወደ ሀገር ገብተው በፖለቲካ ሜዳው የተሳትፎ መብትን ተጎናጽፈዋል። ከፌዴራል እስከ ክልል በካቢኔ እንዲሳተፉም ተደርጓል። ከጽንፍ ፖለቲካ በመራቅ ኅብረ ብሔራዊ አንድነትን የማጠናከር ሥራ ተሠርቷል።

ሕገ መንግሥቱ መንግሥት በሃይማኖት ጉዳይ ጣልቃ አይገባም ሲል ቢደነግግም ከለውጡ በፊት ግን የእምነት ተቋማት የመንግሥት ጥገኛነትና የፖለቲካ ጣልቃ ገብነት ሲያምሳቸው እንደነበር የምናስታውሰው የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው። ዛሬ ይህንን ታሪክ ወደ ማድረጉ ተሸጋግረናል። የእምነት ተቋማት ልዕልና ተከብሯል። ሁሉም የሃይማኖት ተቋማት የነበረባቸውን ጥያቄ ለመመለስ የሚያስችል ሥራ ተሠርቷል። ውጤቱም በተጨባጭ ታይቷል።

በግብርናው ዘርፍ የምግብ ሉዓላዊነትን ለማስከበር በተሠራው ሥራ የተደረሰበት የባሕል ለውጥ ሌላው የለውጡ ቱርፋት ነው። ከዚህ በፊት የዝናብ ወቅት ብቻ ይጠብቅ የነበረው የግብርና ሥራ መስኖና የበጋ እርሻን በመጠቀም፣ ኩታ ገጠም የአስተራረስ ዘዴን በመከተል፣ ቴክኖሎጂዎችን ሥራ ላይ በማዋል ከፍተኛ ምርት ማምረት ተችሏል። በተለይ በስንዴ እና ሩዝ ምርቶች ላይ ልዩ ትኩረት አድርጎ በተሠራው ሥራ ኢትዮጵያ በአፍሪካ ቀዳሚዋ የስንዴ አምራች ሀገር ሆናለች። ከርዳታ ተቀባይነት ወጥታ ወደ ላኪነት ተሸጋግራለች።

የሌማት ትሩፋት የለውጡ ሌላኛው ቱሩፋት ሲሆን ወተት፣ የዶሮና የማር ምርቶች የቤተሰብ ምግብ መሆን ችሏል። በዚህም የዶሮ ሥጋን ምርት ከነበረበት 70 ሺህ ቶን ወደ 208 ሺ ቶን፤ የወተት ምርት ከነበረበት ሰባት ነጥብ ሁለት ቢሊዮን ሊትር ወደ 10 ቢሊዮን ሊትር ደርሷል። የማር ምርት ደግሞ ከ 129 ሺህ ቶን ምርት ወደ 272 ሺህ ቶን ለማሳደግ ተችሏል። አንድም በኢኮኖሚ የማደግ ሌላም ተመጣጣኝ ምግብን የማግኘትና ገበያን በማረጋጋት ያደረገው አስተዋጽኦ ቀላል አይደለም።

ባለፉት ስድስት ዓመታት በተከታታይ ዓለምን ያስደመመ ፤ ተፈጥሮን የለወጠ ፤ ዐሻራን ለትውልድ ያስቀመጠ የአረንጓዴ ልማት ሥራም ተሠርቷል። በዚህም 40 ቢሊዮን የተለያዩ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ያላቸው ችግኞችን መትከል ተችሏል። ይህም 50 ነጥብ 4 በመቶ የደን ዛፍ ፤ 48 ነጥብ 6 በመቶ ዘርፈ ብዙ ጥቅም የሚሰጡ፣ የፍራፍሬ፣ የመኖና የማገዶ የእንጨት ዛፎች ናቸው። ይህም በእያንዳንዱ ግለሰብና ቤተሰብ ባህል ሆኖ ቀጥሏል።

በሀገር በቀል የኢኮኖሚ ሪፎርም በሁሉም መስክ ኢትዮጵያ ወደፊት እየተስፈነጠረች ትገኛለች። በኤክስፖርት ገቢ በኢንዱስትሪ ዕድገት በቴክኖሎጂ ወዘተ የተመዘገቡ ድሎች የዚህ አባባል እውነተኛነት ማረጋገጫዎች ናቸው።

ዛሬ ዓለም የደረሰበት ዲጂታላይዜሽን ዘመን ላይ ቆመን ኢትዮጵያ የበይ ተመልካች እንዳትሆን የለውጡ መንግሥት ወገቡን አስሮ የቴክኖሎጂው ባለቤት ለመሆን ከፍተኛ ጥረት በማድረግ ላይ ይገኛል። በዘርፉ በርካታ ሰዎችን በማሠልጠን ከፍተኛ በጀት በመመደብ በተሠራው ሰፊ ሥራ አስገራሚ ውጤት ተገኝቷል።

የዲጂታል አካውንት ብዛት ከነበረበት 52 ነጥብ 1 ሚሊዮን ዛሬ ወደ 205 ነጥብ 4 ሚሊዮን ደርሷል። በዘመናዊ የክፍያ ዘዴ የተላለፈው የገንዘብ መጠን ደግሞ ወደ 9 ነጥብ 6 ትሪሊዮን ብር አድጓል።

በቱሪዝም ገቢን የሚያሳድጉና የሥራ ዕድል የሚፈጥሩ ሥራዎች ተሠርተዋል። ገበታ ለሸገር ፤ ገበታ ለሀገር እና ገበታ ለትውልድ ፕሮጀክቶች እንዲሁም ኮሪደር ልማቱን ማንሳት ብቻ ከበቂ በላይ ነው። ተበላሽተውና ወደ ውድቀት እያመሩ የነበሩ ታላላቅ ፕሮጀክቶችም በልዩ ክትትል በማጠናቀቅ ለፍሬ በቅተዋል። ለዚህም ታላቁ የህዳሴ ግድብ ዋነኛ ማሳያ ነው።

እንዲሁም የማክሮ ኢኮኖሚ ስብራት ለለውጡ ምክንያት ከሆኑት መካከል የሚጠቀስ ነው። እነዚህንና ሌሎች ያልተጠቀሱ የለውጥ ፍሬዎች ሀገር እንደ ሀገር እንድትቆምና ብልጽግናዋ እንዲረጋገጥ ያደረጉ በመሆናቸው እያጣጣምን ልንጠቀምባቸው፤ የበለጠ አሳድገን የኢትዮጵን ሁለንተናዊ ብልጽግና ልናረጋግጥ ይገባል!


# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ
- አልማዝ አያሌው

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## የጥራት መንደር እና ትሩፋቶቹ

እስማኤል አረቦ

ባለፉት አምስት አመታት ኢትዮጵያ በርካታ እድገቶችን አስመዝግባለች። የግብርና ኋላ ቀርነትን ቀርፎ የምግብ ሉዓላዊነትን ለማስከበር በተሠራው ሥራ የባሕልም የውጤትም ለውጥ መጥቷል። ከዚህ በፊት የዝናብ ወቅት ብቻ ይጠብቅ የነበረው የግብርና ባህል መስኖን በመጠቀም፣ በኩታ ገጠም እርሻና መሬት ጦም እንዳያድር በተሠራው ሥራ፣ ዓመቱን ሙሉ የሚመረትበት ባህል እያመጣ ነው። ስንዴን፣ ሩዝን፣ ገብስን፣ በቆሎንና የፍራፍሬ ምርቶችን ትኩረት አድርጎ በተሠራው ሥራ ኢትዮጵያ በአፍሪካ ቀዳሚዋ የስንዴ አምራች ሀገር ሆናለች።

ግብርና ባለፉት ዓመታት ከፍተኛ ውጤት የታየበት ዘርፍ ነው። ቀደም ሲል ክረምት እና ዝናብ ተጠብቆ ሲሠራበት የነበረው የግብርና እንቅስቃሴ አሁን ወቅት የማይገድበው ሆኗል። በዚህም ምክንያት ሰብል፣ ጥጥ፣ ሆርቲካልቸር ተደምሮ ክረምት ከበጋ ሰላሳ ሚሊዮን ሄክታር መሬት በማረስ 1.4 ቢሊዮን ኩንታል ምርት እንደሚሰበሰብ ይጠበቃል።

በኢንዱስትሪ እና በማዕድን ዘርፎችም በርካታ ውጤቶች ተመዝግበዋል። ወደ ውጭ የሚላኩ የኢንዱስትሪ ምርቶችን ለማበራከት የሚያስችሉ መሠረቶች ከመጣላቸውም ባሻገር ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ ተኪ ምርቶችን በሀገር ውስጥ ማምረት ተችሏል።

ማእድን በሚመለከት በወርቅ፣ ብረታብረት፣ የድንጋይ ከሰል አዳዲስ ፋብሪካዎች ሥራ ይጀምራሉ። በርካታ የወርቅ ፋብሪካዎችም ወደ ሥራ ይገባሉ። ወደ ውጭ ከተላከ ወርቅ ባለፉት ሶስት ወራት ከ500 ሚሊዮን ዶላር በላይ መገኘቱ ብዙዎችን ወደዚህ ዘርፍ እንዲገቡ እንደሚያበረታታቸው ይጠበቃል።

ሲሚቶን ብንወስድ የለሚ ሲሚንቶ ብቻ በዓመት 450 ሺህ ቶን ሲሚንቶ ያመርታል። አሁን ያለውን የሲሚንቶ ምርት 16 በመቶ እድገት ሀገር ውስጥ ያመጣል። እነዚህ ፋብሪካዎች በተሟላ አቅም እየሠሩ ሲሄዱ የኢንዱስትሪው እና የማእድን ዘርፉ ተደምሮ ከፍተኛ እምርታ ያመጣል ተብሎ ይጠበቃል።

ይህም ሆኖ አሁን ከጥራት ጋር የተያያዙ ጉዳች ዛሬም ያልተሻገርናቸው ችግሮቻችን ናቸው ከሀገር የሚወጡ ምርቶች በጥራት ረገድ ጥያቄ የሚነሳባቸው ናቸው። የጥራት መጓደል እንደ አፍሪካ ባሉ ታዳጊ ሀገሮች የንግድ እድሎችን የመፈተሽ፣ በዓለም ገበያ የመወዳደር እና በዓለም አቀፍ የእሴት ሰንሰለት የመሳተፍ አቅም ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ማሳደሩ የማይቀር ነው። በርካታ ኩባንያዎች በንግድ አጋሮች የሚፈለጉትን የጥራት መስፈርቶችን እና የንግድ ደንቦችን ገቢራዊ በማድረግ ረገድ ችግሮች ይገጥማቸዋል።

የጥራት መጓደል በማኑፋክቸሪንግ እና በአገልግሎት አሰጣጥ ላይ ተወዳዳሪነትን በማሳደግ በዓለም አቀፍ የንግድ ለውውጥ ውስጥ እንቅፋት ይሆናል። ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ ምርቶች ተጠቃሚ ጋር ሲደርሱ በርካታ ችግሮች የሚስተዋልባቸው እና ጥቂት ጥቅም ብቻ ሰጥው የሚወገዱ ይሆናሉ።

ይህ ደግሞ በከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ የመጡ ዕቃዎች ተገቢውን አገልግሎት ሳይሰጡ እንዲቀሩ እና ያለውን ጥቂት የውጭ ምንዛሬ አቅም አላግባብ እንዲባክን በር የሚከፍት ነው። በዚህም ላይ በተጠቃሚው ዘንድ ከፍተኛ ምሬትን እና ቅሬታንም ያስከትላል።

ለጥራት ትኩረት መስጠት ፋይዳው የጎላ ነው። የሸማቾች፣ የአምራቾች እና የተቆጣጣሪዎች ጥቅም ለማስጠበቅ ይረዳል። ሸማቾች ጥራት ያላቸውን ምርቶችን ለመምረጥ ያገለግላቸዋል። እውቅና ባለው ላብራቶሪ ተፈትሸው ያለፉ ምርቶች የተወሰኑ በተጠቃሚው ላይ ርካታን ይፈጥራሉ።

አምራቾች ምርቶቻቸው ለገበያ ከመቅረባቸው በፊት ውስንነቶችን በመቅረፍ ከአላስፈላጊ ወጪ ይጠብቃቸዋል። በዓለም ገበያ ለመሳተፍም ዕድል ይፈጥራል፤ መልካም ተሞክሮዎችን ለመቅስም ይጠቅማል፤ በደንበኞች ላይ እምነት ለመፍጠር ያግዛል።

ይህንኑ ከግንዛቤ በማስገባትም የኢትዮጵያ መንግሥት ለጥራት ከፍተኛ ትኩረት ሰጥቷል። ለዚህም ሰሞኑን ተመርቆ ወደ አገልግሎት የገባው የጥራት መንደር አንዱ ማሳያ ነው። ሰሞኑን የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ብሔራዊ የጥራት መንደርን መርቀው በከፈቱበት ወቅት እንደተናገሩት ፤ ብሔራዊ የጥራት መንደር የኢትዮጵያ ማንሠራራት ዘመን ጅማሪ ተደርጎ የሚወሰድ ነው።

**የጥራት መንደር ግንባታው እያደገ ያለውን የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ በእጅጉ የሚደግፍ ነው። በተለይም ወደ ውጭ የሚላኩ ምርቶች ጥራታቸውን ጠብቀው በዓለም ገበያ ውስጥ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ እና የተሻለ የውጭ ምንዛሬ እንዲያስገኙ በር የሚከፍት ነው**

ኢትዮጵያ እውን ያደረገችው የጥራት መንደርም በግብርና፣ በጤና፣ በግንባታና በሌሎች ዘርፍ ጥራት ያለው ምርትና አገልግሎት ለማቅረብ ወሳኝ ነው። የጥራት መንደሩ ለሀገር ውስጥና ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ ምርቶችን ጥራት በማረጋገጥ በምርት ጥራት ጉድለት የሚያጋጥሙ ጉዳቶችን ያስወግዳል፣ ለዜጎችም ጥራቱ የተረጋገጠ ምርትና አገልግሎት እንዲያገኙ ያደርጋል።

የጥራት መንደር ግንባታው እያደገ ያለውን ኢትዮጵያ ኢኮኖሚ በእጅጉ የሚደግፍ ነው። በተለይም ወደ ውጭ የሚላኩ ምርቶች ጥራታቸውን ጠብቀው በዓለም ገበያ ውስጥ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ እና የተሻለ የውጭ ምንዛሬ እንዲያስገኙ በር የሚከፍት ነው።

ለአብነትም የጥራት መንደር ወደ ሥራ ከመግባቱ በፊትም ቢሆን በቡና የተገኘውም ውጤት የኢትዮጵያ መጻኢ ጊዜ ብሩህ መሆኑን የሚያመላክት ነው። ኢትዮጵያ ከብራዚልና ከቬትናም ቀጥሎ ሶስተኛዋ ትልቅ ቡና አምራች ሀገር ለመሆን በቅታለች። ባለፈው ዓመት 1.4 ቢሊዮን ዶላር ከቡና ኤክስፖርት አግኝተናል። በዚህ ዓመት ሁለት ቢሊዮን ዶላር ገደማ ይጠበቃል።

ዘንድሮ ከአራት መቶ ሃምሳ እስከ አምስት መቶ ሺህ ቶን ድረስ ለውጭ ገበያ ለማቅረብ እቅድ ተይዟል። ይህ ዕቅድ ሊሳካ የሚችለው ኢትዮጵያ ጥራቱን የጠበቀ ቡና ወደ ውጭ መላክ ስትችል ነው። ለዚህ ደግሞ በጥራት መንደር የተተከሉ ዘመናዊ መሣሪያዎች አስተዋጽኦ ከፍ ያለ ነው።

በርካታ ኢንዱስትሪዎች በኢትዮጵያ ታምርት ንቅናቄ ወደ ምርት መግባታቸው እና አንዳንዶቹም በአፍሪካ ገበያ የማፈላለግ ሥራ ውስጥ መግባታቸው የኢትዮጵያ ምርቶች በቀጣይ የአፍሪካን ገበያ እንዲገቡ መልካም እድል መፍጠር እንደሚያስችል ይታመናል ። የጥራት መንደር ግንባታውም ኢንዱስትሪዎች ከሀገር ውስጥ አልፈው በውጭው ገበያ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ አቅም የሚፈጠር ሆኗል።

# «ብልጽግና ከጠላትና ወዳጅ የፖለቲካ ሥርዓት...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

የፖለቲካ ሥርዓት ወደ ሃሳብ ልዕልና እና ገንቢ የተፎካካሪ ፖለቲካ መሻገሩን ገልጸዋል።

ፓርቲው ኢትዮጵያ እንዳይገቡ ታግደው የነበሩ የፖለቲካ ኃይሎች በሰላማዊና በሕጋዊ መንገድ የሚታገሉበትን መድረክ ማመቻቸቱን አመልክተው፤ የተፎካካሪ ፓርቲዎች ጋር ለሀገር ግንባታ በጋራ መሥራት እንደሚቻል የተግባር ምሳሌ መሆን እንደተቻለም አስታውቀዋል።

ከዚህ ቀደም የነበረውን የሚዛን መዛነፎችን ብልጽግና በመደመር አዲስ ዕሳቤ ፍትሀዊነት እንዲሰፍን ማድረጉን አንስተው፤ ታሪካዊ ስብራቶች ለመጠገንና ለዘመናት ያልተግባባንባቸውን ጉዳዮች ለመፍታት የሀገራዊ የምክክር ኮሚሽን፣ የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲና የተሀድሶ ኮሚሽን ተቋቁመው እየሠሩ ይገኛሉ ብለዋል።

የብልጽግና ፓርቲ አምስት ዓመታት ጉዞ የብርሃን ፍንጣቂ ጨረር በማሳየት በአጭር ጊዜ በርካታ የልማት ሥራዎች የተሠሩበት መሆኑን ጠቁመው፤ የአዲስ አበባ ከተማ በእነዚህ ጥቂት ዓመታት ያካሄደችው ሁለተናዊ ለውጥ አንዱ ማሳያ እንደሆነ ተናግረዋል።

የልማት ሥራዎቹ ድህነትን ለማሸነፍ ፈርጀ ብዙ ፋይዳዎች ያላቸው ናቸው ያሉት አቶ ተመስገን፤ ግባችን ብልጽግና፤ መንገዳችን ደግሞ በመደመር ዕሳቤ ያሉንን ሀብቶች፣ ባሕሎች ፣ እሴቶችና አቅሞችን ደምረን ታላቅ ሀገራዊ አቅም እንፈጥራለን ብለዋል።

በሀገሪቱ የሰላምና የልማት ሥራዎችን በማጠናከር በዓለም የፖለቲካና የኢኮኖሚ መድረክ ኢትዮጵያ የሚገባትን የመሪነት ሚና መጫወት እንደሚኖርባት አመልክተው፤ ለዚህም ብልፅግና ፓርቲ ያለ ዕረፍት በመሥራት የኢትዮጵያን ሁለንተናዊ ብልፅግና እውን እንደሚያደርግ አስታውቀዋል።

የብልጽግና ፓርቲ ምክትል ፕሬዚዳንት እና በምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ማዕረግ የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ማስተባበሪያ ማዕከል ኃላፊ አቶ አደም ፋራህ በበኩላቸው፤ ብልፅግና ፓርቲ ባለፉት አምስት ዓመታት ውስጥ በእያንዳንዱ የተለያዩ ዓለም አቀፍና ሀገራዊ ፈተናዎች እያለፈ እዚህ የደረሰ ጠንካራ ፓርቲ መሆኑን ገልጸዋል።

ያጋጠሙንን ሁሉንም ፈተናዎች በአሻጋሪ ሃሳብ፣ በአሰባሳቢነትና በብሄራዊ አንድነት ወደ ድል እየቀየርናቸው መጥተናል ብለዋል።

የፎቶ አውደ ርዕዩ የለውጡ ፍጥነት፣ ጥራትና ብዛት፣ የነበሩ ፈተናዎችን እንዲሁም የተመዘገቡ እመርታዎችን የሚያሳይና የሚያስታውስ መሆኑን አንስተው፤ በአራት ዋና ዋና ክፍሎች የቀረበ መሆኑን ገልፀዋል።

በተጨማሪም አውደ ርዕዩ የለውጥ ፍሬዎችና ዛሬ ላይ ሁነን ነገን የምናይበት የብልፅግና ማረጋገጫ ምእራፍን ያካተተ መሆኑን ጠቅሰዋል።

በአውደ ርእዩ የፌዴሬሽን ምክር ቤት አፈጉባዔ አገኘሁ ተሻገርን ጨምሮ የብልፅግና ፓርቲ ከፍተኛ አመራሮችና ከፍተኛ የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎች ተገኝተዋል።

# በጅምር የቆሙ የጤና ተቋማት...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ሊያገኙ የሚገባቸውን የጤና አገልግሎት እያገኙ ባለመሆኑ በተደጋጋሚ ቅሬታዎች እያቀረቡ ይገኛሉ ብለዋል።

ከእነዚህም መካከል በሀረሪ ክልል የሚገኘው የሕይወት ፋና ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል አንዱ እንደሆነ አመልክተው ፤ ከዓመታት በፊት የሆስፒታሉ የማስፋፊያ ግንባታ ተጀምሮ 80 በመቶ ከደረሰ በኋላ ግንባታው መቋረጡን አስታውሰዋል። በዚህም ሆስፒታሉ አገልግሎቱን ባልተጠናቀቀው ማእከል ውስጥ እየሰጠ እንደሚገኝ ተናግረዋል ።

ሆስፒታሉ ለምስራቁ የሀገሪቱ ክፍል ትልቁ ሪፈራል ሆስፒታል ነው ፤ በዓመት ሶስት መቶ ሺህ ለሚደርሱ የካንሰር ህሙማን አገልግሎት የሚሰጥ እንደሆነ ጠቁመው ፤ አገልግሎቱን ከጂቡቲ፤ ከመቋዲሾ፤ ከሀርጌሳ እና ከፑንት ላንድ ለሚመጡ ታካሚዎች እንደሚሰጥም ገልጸዋል። በተመሳሳይ በክልሉ እየተገነባ ያለው የላብራቶሪ ማእከልም ግንባታው 80 በመቶ ደርሶ መቆሙን አመልክተዋል።

በተመሳሳይ በደቡብ ክልል ወላይታ ዞን በቦዲቲ ከተማ አስተዳደር በጤና ሚኒስቴር በኩል የመጀመሪያ ደረጃ ሆስፒታል በ2008 ዓ.ም ለመገንባት የመሠረት ድንጋይ ተቀምጦ ፣ የህንጻ ግንባታ ቢጀመርም እስካሁን አለመጠናቀቁን አንስተዋል። ግንባታው በተደጋጋሚ ጥያቄ ቢቀርብበትም ሊጠናቀቅ አለመቻሉን የምክር ቤቱ አባላቱ ጠቁመዋል።

በኦሮሚያ ክልል የባኮ ሆስፒታል ከመጀመሪያ ደረጃ ሆስፒታል ወደ አጠቃላይ ሆስፒታል ይደግልን ጥያቄ በአካባቢው ባለው ማህበረሰብ በተደጋጋሚ መነሳቱን ያስታወሱት አባላቱ ፤ የአካባቢው ነዋሪ ለወባና ተያያዥ በሽታዎች በስፋት ተጋላጭ መሆኑ ፤ ከዛም ባለፈ ሆስፒታሉ በርካታ ወረዳዎችን የሚሸፍን ከመሆኑ አኳያ የማህበረሰቡ ጥያቄ ፈጣን ምላሽ ማግኘት እንዳለበት አመልክተዋል።

በአሁኑ ወቅት ግን አብዛኛው ነዋሪ ወደ ሌሎች አካባቢዎች ለህክምና እየተንቀሳቀሰ ለበርካታ እንግልቶችና ለከፍተኛ ወጪ እየተዳረገ ይገኛል። እንዲህ አይነት ችግሮች ከተጠቀሱትም ባለፈ በሌሎችም አካባቢዎች እንዳሉ አባላቱ አንስተው፤ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ምላሽ እንዲሰጣቸው ጠይቀዋል።

የጤና ሚኒስትሯ ዶክተር መቅደስ ዳባ ከምክር ቤቱ አባላት ለቀረቡላቸው ጥያቄዎች በሰጡት ምላሽ፤ ጥያቄዎቹ ተገቢ ናቸው። ከዚህ ቀደምም በተለያየ አግባብ ቀርበዋል። በጅምር የቆሙ የጤና ተቋማትን ወደ ሥራ የማስገባት ሥራ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ቅድሚያ ሰጥቶ በትኩረት እየሠራባቸው ካሉ ጉዳዮች መካከል ናቸው ብለዋል።

በአሁኑ ወቅት እንደ ሀገር ያሉት አብዛኛዎቹ ትልልቅ ሆስፒታሎች ከሃምሳ ዓመት በላይ የቆዩ ናቸው ፤ እነሱን የማደስና የግብዓት የማሟላት ሥራዎችን መሥራት ያስፈልጋል ያሉት ሚኒስትሯ ፤ባለፈው ሩብ ዓመት 140 የጤና ኤክስቴንሽን የሚሰጡ ኬላዎች ወደ ሥራ ገብተዋል። አንድ ሺህ 986 ጤና ኬላዎችን ከጤና ጣቢያዎች ጋር በማቀናጀት ደረጃቸውን ማሳደግ መቻሉን ገልጸዋል

ግጭት በነበረባቸው የሀገሪቱ አካባቢዎች የነበሩ 251 የህክምና ተቋማትን ቀድሞ ከነበሩበት በተሻለ መልኩ በሙሉ አቅማቸው ወደ ሥራ እንዲገቡ እየተሰራ ነው ፤ ከዚህ በተጨማሪም የላብራቶሪ አገልግሎትና የመድሃኒት አቅርቦትን በሀገር ውስጥ ምርት ለመሸፈን በርካታ ሥራዎች እየተሠሩ መሆኑን ጠቁመዋል።

# አሳሳቢውን የሳይበር ጥቃት...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ይህ አሀዝ ወደ 8ሺ854 ከፍ ብሏል። አሃዞቹ የሳይበር ጥቃት ከዓመት ወደ ዓመት እያሻቀበ መምጣቱን ያመላክታሉ።

በመንግሥት በኩል የሳይበር ደህንነት ተጋላጭነትን ለመቀነስ እየተሠራ ነው። ለጥቃቱ የተጋለጡ ተቋማትን በመለየትና መፍትሄ በማመላከት እንዲሁም ግንዛቤ በማስጨበጥ ላይ በመሥራት ችግሩን ለመቀነስ እየተሞከረ ይገኛል። በተለይ ቁልፍ መሠረተ ልማቶች ላይ ትኩረት በማድረግ ተጋላጭነቱን ለመቀነስ እየተሠራ ስለመሆኑ በቅርቡ የሳይበር ወር በተከበረበት ወቅት ተጠቁሟል።

የዘርፉባለሙያዎችችግሩንለመቀነስብዙመሥራት እንደሚያስፈልግ ያመለክታሉ። በኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር የብሔራዊ የኔትወርክ ማሳለጫ ቡድን መሪ አቶ ዳንኤል አድነው የሳይበር ደህንነት በበይነ መረብ (ኢንተርኔት) አማካኝነት በሚደረጉ ግንኙነቶች የተለያዩ አገልግሎቶችን በማግኘት ሂደት የሚገጥሙ ተጋላጭነቶች መሆናቸውን ይገልጻሉ። ከእነዚህ አገልግሎቶች የተወሰኑት ሀገር ውስጥ የሌሉ መሆናቸውን በመጥቀስም፣ አገልግሎቶቹን ፍለጋ ወደ ውጭ ሲወጣ ተጋላጭነቱ እንደሚከሰት ይናገራሉ።

ይህንንም አብነት ጠቅሰው ሲያብራሩ እንዳሉት፤ ሰዓት ለማስተካከል ሲባል ወደ ውጭ ሀገር መውጣት ያስፈልጋል። ይህንንና መሰል አገልግሎቶች ፍለጋ ወደ ውጭ በሚወጣበት ጊዜ ሳይበር ተጋላጭነት ይጨምራል።

ሌሎች ሀገራት በሀገር ውስጥ የጊዜ መቆጠሪያ ሰዓት ማስተካከያ አገልግሎት አላቸው። ደቡብ አፍሪካ 48 ፣ኬንያ 6 ፣ ሶማሊያ 4 እና ጂቡቲም 2 ያህል የሰዓት ማስተካከያ በሀገር ውስጥ እንዳላቸው ጠቅሰው፤ኢትዮጵያ ግን ይህ የሰዓት ማስተካከያ አገልግሎት የላትም። ይህንን እና መሰል የሌሉ አገልግሎቶችን በሀገር ውስጥ ለማምጣት በኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ብሔራዊ የኔትወርክ ማሳለጫ ፕሮጀክት እየተሠራ መሆኑን ይጠቅሳሉ።

እሳቸው እንደሚሉት፤ ይህ ፕሮጀክት ሥራ ላይ ሲውል አሁን እንደ ሀገር እየተከሰተ ያለው የሳይበር ተጋላጭነትን 60 በመቶ መቀነስ ፣ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪን ለማስቀረት እና የኢንተርኔት ፍጥነት በከፍተኛ ደረጃ ሁኔታ ለማሻሻል ይረዳል።

ሀገር ውስጥ የሌሉ አገልግሎቶች ፍለጋ ወደ ውጭ በምንወጣበት ወቅት የበይነ መረብ ትራፊክን በማሳለጥም በ80 በመቶ ያህል ሀገር ውስጥ ለማስቀረት ያስችላል። በ20 በመቶ ያህል ብቻ ወደ ውጭ በመውጣት የሳይበር ተጋላጭ እንዳንሆን ኦዲት ለማድረግ ይጠቅማል። አነስተኛ የትራፊክ ፍሰት ሲኖር ሳይበር ደህንነት ተጋላጭነት ለመቀነስ ይረዳል።

ዋና ዋና ኢንተርኔት መሠረተ ልማቶችን ለመጠቀም መቶ በመቶ የበይነ መረብ (ኢንተርኔት) ትራፊክ ከሀገር የሚወጣባቸው ሁኔታዎች እንዳሉ አቶ አድነው ይጠቁማሉ፤ ይህንን ከፍተኛ የሆነ ፍሰት ኦዲት ለማድረግ በጣም አስቸጋሪ መሆኑን ጠቅሰው፣ ሁኔታው ተጋላጭነቱ ከፍ እንዲል እንደሚያደርገው ያስረዳሉ።

በሌላ በኩል አሁን እንደ ሀገር የምንጠቀምበት የኢንተርኔት ፕሮቶኮል (IPV4) ለሳይበር ተጋላጭነቱ ከፍተኛ ነው የሚሉት አቶ ዳንኤል ፣ የቀጣዩ ትውልድ ኢንተርኔት ፕሮቶኮል (IPV6) የሚባለው የአፍሪካ ሀገራትን ጨምሮ አብዛኛው ሀገራት እየተጠቀሙበት መሆኑን ይገልጻሉ። ይህ አዲሱ የኢንተርኔት ፕሮቶኮል ደህንነቱ የተጠበቀና በጣም ፈጣን ነው ሲሉም ጠቅሰው፣ በዚህም ተጋላጭነቱን 60 በመቶ መቀነስ ይቻላል ብለዋል። ቀሪውን 40 በመቶ ደግሞ በተለያዩ መንገዶች መከላከል እንደሚቻል አብራርተዋል።

ሳይበር ደህንነት ለማስጠበቅ የሠለጠነና ብቁ የሰው ኃይል እንደሚያስፈልግ ገልጸው፤ አገልግሎቶች የሚሰጡ ተቋማት፣ ዩኒቨርሲቲዎች፣ ኢኖቬሽን ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር፣ የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር (ኢንሳ) ጨምሮ የቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩቶች በሳይበር ደህንነት ላይ ጥናትና ምርምር ሊያደርጉ ያስፈልጋል ይላሉ።

የኤሌክትሪካልና ኮምፒዩተር ኢንጂነሪን ባለሙያ አቶ አማረ ደሳለኝ በበኩላቸው እንደሀገር ያለንበት ሁኔታ የሳይበር ደህንነት ከማስጠበቅ አኳያ ካሉት የሳይበር ስጋቶች አንጻር ሲታይ በጣም ወደ ኋላ ቀርተናል ሲሉ ይናገራሉ።

እሳቸው እንደሚሉት፤ አሁን የሳይበር ደህንነት ለመጠበቅ እየተከናወኑ ያሉ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች ቢኖሩም፣ እንደ ሀገር የጥቃቱ መጠን በየዓመቱ እየጨመረ መጥቷል። የቴክኖሎጂ ተጠቃሚዎች እየበዙ አገልግሎቶችና አሠራሮች እየዘመኑ መሆናቸው ተጋላጭነት በዚያው ልክ እየጨመረ እንዲመጣ እያደረገ ነው።

የሳይበር ደህንነት ለማስጠበቅ ግልጽ የሆኑና ሊተገበሩ የሚችሉ ፖሊሲዎች ሊኖሩ ይገባል የሚሉት አቶ አማረ፤ የምንጠቀማቸው ሶፍት ዌሮችም ሆኑ ፤ ሌሎች ተጋላጭነትን ሊጨምሩ የሚችሉት ደህንነት የተጠበቀ ማድረግ ይኖርብናል ነው ያሉት።

የመንግሥትም ሆነ የግል ድርጅቶች ለሠራተኞቻቸውግንዛቤንማስጨበጥይጠበቅባቸዋል። ጥቃቱ ሳይደርስ አስቀድሞ መከላከልና ጥቃቱ ሲደርስ እንዴት መከላከል ይቻላል በሚለው ላይ ፖሊሲ ሊኖራቸው እንደሚገባም አመልከተው፣ ይህ ሲደረግ የሳይበር ደህንነት እየተጠበቀ ስጋቶችም እየተቀነሱ ሊመጡ ይችላሉ ሲሉ አስረድተዋል።

ሌሎች ሀገራት ኢትዮጵያ የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር እንዳላት ሁሉ የሳይበር ደህንነት የሚከላከል ኤጀንሲ እንዳላቸው ጠቅሰው፣ በኤጀንሲዎቻቸው አማካኝነት የሚጠቀሙባቸውን ፖሊሲዎች በመቅረጽ መቶ በመቶ የሳይበር ደህንነትን ማረጋገጥ ባይችሉም ደህንነት ለመጠበቅ ጥረት እያደረጉ መሆናቸውን ይገልጻሉ።

ቴክኖሎጂዎች በምን እንደሚሠሩና የሳይበር ደህነነቱ የተረጋገጠ ስለመሆኑ ክትትል ማድረግን ይጠይቃል የሚሉት አቶ አማረ፤ ያ የደህንነት ተቋም ያስቀመጠው መስፈርት የሚያሟላ መሆኑን መቆጣጠር ሲቻል የደህንነቱን ስጋት በብዙ መልኩ መቀነስ እንደሚቻል ይገልጻሉ። የኢንፎርሜሽ መረብ ደህንነት አስተዳደር እንደዚህ አይነት ሲስተሞች ላይ ጥብቅ ቁጥጥርና ክትትል የማያደርግ ከሆነ ከፍተኛ ጉዳት ሊከሰት እንደሚችል አመላክተዋል።

የሳይበር ጥቃት አይነቶች ስለሚለያዩ በተለይ አዳዲስ ክስተቶች ቀድሞ በማሳወቅ ግንዛቤ መፍጠር እንደሚያስፈልግ ገልጸው፤ ተከታታይነት ያላቸው የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች በስፋት ሊሠሩ እንደሚገባ አስገንዝበዋል።

የዓለም ኢኮኖሚክ ፎረም መረጃ እንደሚያመላክተው፤ በቀጣይ አስር ዓመታት በዓለም ላይ ከሚከሰቱ ከፍተኛ አደጋዎች መካከል ከአየር ብክለት፣ ከሀሰተኛ መረጃ ስርጭት፣ ከአክራሪነትና ከኑሮ ውድነት በመቀጠል በአምስተኛ ደረጃ የዓለማችን ስጋት ተብሎ የተቀመጠው የሳይበር ጥቃት ሆኗል። የሳይበር ጥቃት ባሕሪው ዓለምአቀፍና ድንበር የለሽ በመሆኑ የዓለም ሀገራት ሁሉ ስጋት እንደሆነ ቀጥሏል።

የሳይበር ደህንነት ስጋት እየጨመረ መምጣቱን ተከትሎ በዓለም አቀፍ ደረጃ የሳይበር ጥቃቶች የሚያስከትሉት ኪሳራ ተበራክቷል። በዓለም በሳይበር ጥቃት እ.ኤ.አ በ2022 የስምንት ነጥብ 44 ትሪሊዮን ዶላር ኪሳራ ደርሷል፤ እ.ኤ.አ በ2027 በዚሁ ጥቃት ሊደርስ የሚችለው ጥቃት ከፍተኛ መሆኑ እየተገለጸ ነው፤ በዚህ ጥቃት ብቻ ሊደርስ የሚችለው ኪሳራ ወደ 23 ነጥብ 84 ትሪሊዮን ዶላር ይሆናል ተብሎ ተገምቷል። ይህን ኪሳራ ከወዲሁ ለመከላከል በጉዳዩ ላይ በትኩረት መሥራትን ይጠይቃል።

ማህበራዊ

# ወጣቶች

## አደራን በየቤቱ የሚያደርሰው ወጣት

**ሰሚራ በርሀ**

ወጣት አስናቀ ጥበቡ ይባላል። በአካባቢው ያለውን ክፍተትን በማጥናት ከጓደኛው ጋር በመሆን በመሠረተው ተቋም ለብዙዎች አገልግሎት ከመስጠት ባሻገር በስሩ ለሚገኙ ሠራተኞች የሥራ እድል መፍጠር ችሏል። እ.አ.አ 2014 የተመሠረተው (Angles Ethiopian Gift Delivery) ውስጥ አስናቀ ሥራ አስኪያጅ ነው። ኤንጅልስ ኢትዮጵያ በዋናነት የሚሠራው ሥራም ሰዎች በጊዜ መጣበብ እና በቦታ ርቀት ምክንያት ለወዳጆቻቸው መስጠት ያልቻሉትን ስጦታ በወኪል ስጦታውን ማድረስ ነው። ‹‹በእኛ ውክልና ውስጥ ፍላጎቶን እናደርሳለን›› ተቋሙ ራሱን የሚገልጽበት ርዕስ ነው።

ሰዎች በቀደመው ጊዜ አንድ እቃ በሰዎች መልካም ፍቃድ አማካኝነት እግረ መንገዳቸውን እንዲያደርሱላቸው ያደርጋሉ፤ ምላሹም ምስጋና እና ወዳጅነት ሊሆን ይችላል። ታዲያ ይህ ሃሳብ ወደ ሥራ እድል መቀየሩ ሊያስገርም ይችላል። ‹‹ያለንበት ጊዜ ብዙ አገልግሎቶችን ለማግኘት ቀላል ያደረገበት ጊዜ ነው። ነገር ግን በዛው ልክ ደግሞ በተለመደው እና ነባር በሆነው የማህበራዊ ግንኙነቶቻችን ላይ የራሱን የሆነ ተጽዕኖ አሳድሯል። ኤንጅልስ ጊፍት ያንን ክፍተት ለመሙላት የተቋቋመ ነው። ››

ሰዎች የሚፈልጉት ማንኛውንም እቃ ለመሸመት ሲፈልጉ እቃው ወደሚገኝበት የገበያ ማዕከል ላይ በመሄድ የሚፈልጉትን እቃ ይገዛሉ። አሁን ባለንበት ዘመን ደግሞ ሰዎች የሚፈልጓቸውን እቃዎች በቤታቸው ሆነው ደውለው በማዘዝ አልያም ቴክኖሎጂው በፈጠረው እና ነጋዴዎቹ በራሳቸው ማህበራዊ ገጾች ላይ የሚሸጧቸውን እቃዎች በማስቀመጥ እቃውን መግዛት ለሚፈልጉ ደንበኞቻቸው አስቀድመው ክፍያ በመቀበል ያሉበት ድረስ ይዘውላቸው ይሄዳሉ።

ይህ ሲሆን ገዢው ቦታው ድረስ በመሄድ የሚታጠፋውን ጊዜ የሚቀንስ ሲሆን ለሻጩ ደግሞ ለሚሸጠው እቃ ከሚጠይቀው ክፍያ ባሻገር እንደሚኖረው አሠራር ቦታው ድረስ በመውሰዳቸው ተጨማሪ ገቢን ያገኛሉ። እቃዎችን ከባለቤቱ ተቀብሎ ከሚመለከተው ሰው ማድረስ አሁን ላይ ራሱን የቻለ ሥራ ሆኗል። ሰዎች በሚኖሩበት ከተማ ውስጥም ሆነው እቃዎችን፣ ሰነዶችን ይህንን ሥራ በሚሰሩ ሰዎች አማካኝነት ይልካሉ። በአብዛኛውም የሞተር ሳይክል ትራንስፖርት ለዚህ ሥራ በስፋት ጥቅም ላይ ይውላል።

ወጣት አስናቀ ትምህርቱን ያጠናቀቀው በኢኮኖሚክስ ሲሆን አንድን የንግድ ሥራ ለመጀመር በአካባቢያችን ያለን ክፍተት ማየት ለሥራ ፈጠራ ጥሩ የሃሳብ መነሻ መሆኑ ያገዘው ይመስላል። ‹‹አንድን እቃ ለሚፈለገው ሰው ማድረስ እና ስጦታን ለሚሰጠው ሰው ማድረስ ይለያያል። ስጦታውን መስጠት የፈለገው ሰው በአካል ቢኖር ለተቀባዩ ሊፈጥረው የሚችለውን ስሜት በሚፈጥር መልኩ አቀራረብ ሊኖረው ይገባል። ›› ይህም ሰዎች ባልጠበቁበት ሰዓት ደስታ የመፍጠር ያክል ይዘት ይኖረዋል።

በመሆኑም ሰዎች ባላቸው የጊዜ መጣበብ፣ ከቦታ ርቀት እና በሀገር ውስጥ ካለመኖር የተነሳ ስጦታዎችን በእነዚህ አማካኝነት ይልካሉ። ‹‹ ሰዎች በተለያየ አጋጣሚ ልዩ ለሚሉት ቀን በአካል መገኘት ባይችሉ ከወዳጆቻቸው ጋር ባላቸው ግንኙነት ማስታወስ በሚፈልጓቸው ቀናት ላይ ስጦታ በመላክ መልካም ምኞታቸውን መግለጽ፣ ቀኑን ማስታወስ ሲፈልጉ እነሱን ወክለን ስሜታቸውን ሊገልጽ በሚችል መልኩ ስጦታቸውን በቀኑ እና በሰዓቱ እናደርሳለን። ›› ይላል ወጣት አስናቀ።

ስጦታዎች ለልደት፣ ለጋብቻ በዓል፣ ለምርቃት እና ለተለያዩ በዓላት በማስመልከት ሰዎች ስጦታቸውን በዚህ ውክልና ያደርሳሉ። ሥራውን በጀመረበት ወቅት በአብዛኛው ከሀገር ውጭ ያሉ ኢትዮጵያዊ ደንበኞችን በስፋት እንዳሉት የሚያስታውሰው ወጣት አስናቀ በአሁኑ ወቅትም በሀገር ውስጥ ያለው አቀባበል ከፍ ያለ መሆኑን ጠቅሷል።

‹‹የኮቪድ-19 ወረርሽኝ ከመከሰቱ በፊት ከተለያዩ ድርጅቶች ጋር አብረን ስለምንሰራ በሀገር ውስጥ ካሉ



ኤምባሲዎች ጋር የመሥራት እድሉ ነበረን። በኋላ ግን የነበሩ የተለያዩ ግንኙነቶች በመቀዛቀዛቸው በሀገር ውስጥ ያለውን ፍላጎት በድጋሚ በማጥናት አስፈላጊ እንደሆነ ሌሎች ደንበኞችን ወደማፍራት ገብተናል።›› ሲሉ ኮቪድ ፈጥሮት የነበረውን ችግር የተሻገረበትን መንገድ ይገልጻል።

የሥራው ባህሪ በብዛት ከደንበኞች ጋር በአካል ከመሆን ይልቅ በማህበራዊ ገጽ ላይ በሚደረጉ የሃሳብ ልውውጦች እንደሚያልቅ የሚገልጸው አስናቀ አብዛኛው የክፍያ መንገድ ጊዜው የፈጠራቸው የኦንላይን የክፍያ መንገዶች አማካኝነት ይፈጸማል። ‹‹ከደንበኞቻችን ጋር በአካል የምንገናኝበት አጋጣሚ ጠባብ ነው። የሚፈልጉትን የስጦታ ዓይነት እና ጥቅል ከነገሩን በኋላ ለክፍያ እንዲመች አሁን ላይ የሚገኙ የተለያዩ የባንክ አማራጮችን በመጠቀም ለደንበኞች ምቹ ለማድረግ እንጥራለን። ›› ሲል አሠራራቸውን ያብራራል።

የስጦታ ትንሽ የለውም የሚባለው የሀገራችን ብሂል እንዳለ ሆኖ ስጦታን በውክልና ለወዳጅ እንዲደርስ ማድረግ ክፍያው ምን ያህል ነው በሚል ወጣት አስናቀ የክፍያ ተመጣጣኝነቱን ጠይቀነዋል። ‹‹በአብዛኛው ተደራሽ የምናደርጋቸው ደንበኞቻችን መካከለኛ ገቢ ላይ ያሉ የምንላቸውን ነው። ከምንታዘዘው የስጦታ ዓይነት ባሻገር ስጦታውን ለማድረስ የምናወጣውን የትራንስፖርት ክፍያ አማካኝ የምንለውን አድራሻ በመለየት ተመጣጣኝ ክፍያ እንጠይቃለን። ከዚያም ደግሞ ከአገልግሎት ክፍያ በተጨማሪ በክፍያ ሥርጭቱ ላይ የሚጠቃለል ይሆናል። ›› በማለት ተደራሽ ለማድረግ ያሰቧቸውን የማህበረሰብ ክፍል እና ክፍያ አብራርቷል።

አንድ ደንበኛ ስጦታ ለመላክ ኤንጅልስ ቢፈልግ ስጦታው እንዲላክ ከሚፈልግበት አንድ ቀን አስቀድሞ የስጦታ ዓይነት ጥቅሎች ተመርጠው የሚጠናቀቁ ሲሆን የክፍያ ሁኔታውም በዚህ መልኩ ይከናወናል።

አስናቀ በሥራ አጋጣሚ ላይ የሚገጥሙ በርካታ ገጠመኞች መኖራቸውን ያስረዳል። ሰዎች ስጦታዎችን ለሰው ለመስጠት የመረጡትን ልዩ ቀን እንደ ምክንያት ይጠቀማሉ፤ ታዲያ የታዘዘው ስጦታው በተባለው ቦታ ልክ በቀኑ እና በሰዓቱ ሊደርስ ይገባል። አስናቀ ከዚህ ጋር ተያይዞ ያለውን

**‹‹አንዳንድ ጊዜ የምንጠቀማቸው የኦንላይን የክፍያ ሥርዓቶች የመዘግየት ሲስተም ያለመሥራት ነገር ይኖራል። በዚህ ወቅት እንደ አማራጭ የምንወስደው ብቸኛው ነገር እምነት ነው ››**



ገጠመኝ እንዲህ አጋርቶናል። ‹‹አንዳንድ ትእዛዞቻችን የተቆረጠ ሰዓት የተቀመጠላቸው ይሆኑና የሚኖረውን የመንገድ መጨናነቅ መገመት አንችልም እና ቅርብ ነው ብለን የምናስባቸው አድራሻዎች ራሱ መድረስ የማንችልበት ሁኔታዎች ይፈጠራሉ። በዚህ ምክንያት ብዙ ገጠመኞች አሉን። ›› ሲሉ በዚህ ረገድ በርካታ ገጠመኞች መኖራቸውን ያስረዳል። ሆኖም ማንኛውንም የታዘዙ ስጦታዎች ከታዘዙበት አንድ ሰዓት ቀድመው ወደ ቦታው የመንቀሳቀስ ሥራቸውን እንደሚጀምሩ ያስረዳል።

‹‹አንዳንድ ጊዜ የምንጠቀማቸው የኦንላይን የክፍያ ሥርዓቶች የመዘግየት ሲስተም ያለመሥራት ነገር ይኖራል። በዚህ ወቅት እንደ አማራጭ የምንወስደው ብቸኛው ነገር እምነት ነው። ›› በማለት አገልግሎቱን በመስጠት እና ደንበኞችን ባለመግፋት ከአገልግሎት በኋላ ክፍያ ይጠይቃሉ በዚህም ክፍያውን ያልፈጸሙ እምነት/ታማኝነት ያጎደሉ ደንበኞች አልመኖራቸውን አስናቀ ያስታውሳል።

ኤንጅልስ ኢትዮጵያ ከተመሠረተ ከ10 ዓመት በላይ አስቆጥሯል። አስናቀ ከዚህ በኋላ ኤንጅልስ ኢትዮጵያ በተሻለ መልኩ ሌሎች ጋር እንዲደርስ የማድረግ እቅዶች አሉት። ከሚሠራቸው ሥራዎች ባሻገር የተለያዩ የስጦታ ጥቅሎችን በራሱ በማዘጋጀት ለደንበኞች ማቅረብ ይፈልጋል።

ሥራውን በተጀመረበት ወቅት ከጓደኛው ጋር በመሆን ባዘጋጁት ይፋዊ ድህረ ገጽ ትእዛዞችን በመቀበል፣ ማስታወቂያዎችን በመሥራት ጀምረውታል። ‹‹አብዛኛው ሥራችን የታዘዘውን ስጦታ ማድረስ ሲሆን ይህንን ሥራ የሚያከናውኑልን ቋሚ እና ትእዛዝ ቁጥራችን በሚበዛበት ወቅት የምናሰማራቸው ሠራተኞች አሉን። ›› ይህም የሚሆነው የበዓላት ወቅት ላይ የሚኖረው የትእዛዝ ፍላጎት የሚጨምር መሆኑን አስናቀ ይገልጻል።

ከጓደኛው ጋር በመሆን የጀመረው የሰዎችን ስሜት እና ፍላጎት ተከትሎ ሰዎች የጎደሉበትን ቦታ መሙላት ሥራ አሁን ላይ በሀገር ውስጥ ሰዎች ተቀባይነት ማግኘቱን የሚገልጸው ወጣት አስናቀ ማንኛውንም ሥራ ወጣቶች ለመጀመር ከማሰባቸው በፊት ምን ክፍተት አለ የሚለውን መፈተሽ ይኖርባቸዋል በማለት ይገልጻል። ‹‹በሀገር ደረጃ ምን ችግር ወይም ክፍተት አለ የሚለውን መረዳት ያስፈልጋል። ክፍተቱን ከለዩ በኋላ ይህንን ክፍተት በመሙላት እንዴት ትርፍ ማግኘት ይቻላል የሚለው ተከትሎ የሚመጣ ጥያቄ ነው። ›› በመሆኑም አካባቢን እና ነባራዊ ሁኔታን ማጥናት አንዱ ሥራ የመፍጠሪያ መንገድ መሆኑን ጠቅሷል። በመረጡት የሥራ ሃሳብ ላይ ደግሞ ራሳቸውን ማብቃት ይጠበቅባቸዋል።

‹‹አሁን ላይ ያለንበት ወቅት ደግሞ የተለያዩ ጥናቶችን ኢንተርኔቶችን በመጠቀም በቀላሉ ጥናት ማድረግ መረጃዎችን ማግኘት ይቻላል። ›› በማለት ጊዜው ያመጣቸው እድሎችን በመጠቀም የሥራ ሃሳቦች ማግኘት ብቻ ሳይሆን ወጣቶች ራሳቸውን ማብቃት ጭምር ይህንን መንገድ ይችላሉ።

# ማዕድናትን ማስተዋወቅና የገበያ ትስስር መፍጠር ያስቻለው ኤክስፖ

**ወርቅነሽ ደምሰው**

ሦስተኛው ዓለም አቀፍ የማዕድንና ቴክኖሎጂ «ማይንቴክ ኤክስፖ» በቅርቡ በሚሊኒየም አዳራሽ መካሄዱ ይታወቃል። የማዕድን ድግስ በሚል ሊገለጽ በሚችለው በዚህ ኤክስፖ፣ ለማየት የሚያሳሱ፤ ታይተው የማይጠገቡ እጅግ የሚያምሩና ውብ የከበሩና የጌጣጌጥ ማዕድናት፣ ወርቅ ፣ የድንጋይ ከሰል፣ ለኢንዱስትሪና ለኮንስትራክሽን ግብዓትነት የሚውሉ እና ሌሎች ማዕድናት በየዓይነት በዓይነት ቀርበዋል። እነዚህ ሁሉ ማዕድናት እውን በኢትዮጵያ የሚገኙ ናቸው ብለን ራሳችን እንድንጠይቅ የሚያደርጉ ስማቸውን ሰምተንም ሆነ አይተናቸው የማናውቃቸው ብዙ ዓይነት ማዕድናት ቀርበው ተጎብኝተዋል።

ከኅዳር 13 እስከ ኅዳር 17 ድረስ ለአራት ቀናት በተካሄደው በዚህ ኤክስፖ ላይ የመንግሥት አካላት፣ በማዕድን ዘርፉ የተሰማሩ በርካታ አልሚዎች፣ እሴት ጨማሪዎች፣ ገዥዎች፣ ላኪዎችና በርካታ የሀገር ውስጥና ዓለም አቀፍ ጎብኚዎችም ተገኝተዋል።

ማዕድናትን ማስተዋወቅ፣ ለማዕድን ምርቶች የገበያ ትስስር መፍጠር፣ ቴክኖሎጂ ማሳየትና ማስተዋወቅም በስፋት በታየበትና በማዕድን ዘርፉ መልካም እድሎች፣ ፈተናዎችና መፍትሔዎች እንዲሁም ስኬቶች ላይ የተለያዩ መድረኮች በተካሄዱበት በዚህ ኤክስፖ መክፈቻ ላይ ፕሬዚዳንት ታዬ አፅቀ ሥላሴን ጨምሮ ሌሎች ከፍተኛ ባለሥልጣናት ተገኝተዋል።

የኢፌዴሪ ፕሬዚዳንት ታዬ አፅቀ ሥላሴ ኤክስፖውን በከፈቱበት ወቅት ኢትዮጵያ ያላትን እምቅ የማዕድን ሀብት በዘመናዊ መንገድ አልምቶ መጠቀም የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋት እንደሚገባ አስታውቀዋል። ሀገሪቱ ያሏትን የማዕድን ሀብቶች ለመለየት፣ ለማልማትና ለመጠቀም ዘመናዊ ሥርዓትን መከተል እና ቴክኖሎጂዎችን መጠቀም እንደሚገባ አመልክተው፤ በዘርፉ የተሰማሩ ባለሀብቶችም የእውቀት ሽግግር ለማድረግ የሚያስችሉ ቴክኖሎጂዎችን በስፋት መጠቀም እንዳለባቸው ገልጸዋል።

ፕሬዚዳንቱ እንደሚሉት፤ የማዕድን ሀብት የውጭ ምንዛሬ ገቢን ለማሳደግ፣ በአጠቃላይ ለሀገሪቱ ኢኮኖሚያዊ እድገት ወሳኝ ነው። የማዕድን ዘርፉን ለማልማት ከመንግሥት በተጨማሪ ባለሀብቶች እና ባለድርሻ አካላት እገዛ ሊያደርጉ ይገባል። ፕሬዚዳንቱ ኤክስፖውን ጎብኝተዋል።

በኤክስፖው ከተሳተፉት መካከል በድንጋይ ከሰል ልማት የተሰማራው «ጂሚቲ የድንጋይ ከሰል አምራች ድርጅት» አንዱ ነው። ድርጅቱ በኦሮሚያ ክልል ጅማ ዞን ጦላይ የሚባል አካባቢ የሚገኝ ሲሆን፣ ከተቋቋመ ሦስት ዓመታትን አስቆጥሯል። ድንጋይ ከሰል በማምረት ለሲሚንቶና ብረት ፋብሪካዎች ያቀርባል።

የድርጅቱ የሽያጭ ባለሙያ አቶ ዳዊት ኪቲላ እንደሚለው፤ ድርጅቱ ከውጭ ሀገራት በከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ የሚገባውን የድንጋይ ከሰል በሀገር ውስጥ ለመተካት ታስቦ የተቋቋመ ነው። በተፈጥሮ የሚገኘውን የድንጋይ ከሰል የሚያመረት ሲሆን፣ ከአራት ሺ 500 እስከ 5000 ኮሎሪ መጠን ያለው የድንጋይ ከሰል ያመርታል። በቀን ከሶስት ሺ ቶን በላይ የድንጋይ ከሰል እያመረተ በተመጣጣኝ ዋጋ ለፋብሪካዎች ያቀርባል።

ድርጅቱ ቀደም ሲል ከውጭ በከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ይገባ የነበረው የድንጋይ ከሰል በሀገር ውስጥ እያመረተ መሆኑን ጠቅሶ፤ የድንጋይ ከሰልን በሀገር ውስጥ ማምረት መቻል እንደ ሀገርም ያለው ፋይዳ ከፍተኛ መሆኑን አመላክቷል።

በኤክስፖው ድርጅቱ የሚያመርተውን የድንጋይ ከሰል ይዞ መቅረቡ ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ እንዳለው ጠቅሶ፣ በተለይ የገበያ ትስስር ለመፍጠር እንደሚያስችለው ይገልጻል። ኢትዮጵያ በርካታ የማዕድን ዓይነቶች ያላት ስለመሆኗ ግንዛቤው የሌላቸው ብዙ ሰዎች እንዳሉ ተናግሮ፣ ባለሀብቶች ከድርጅቱ ጋር መሥራት የሚችሉባቸው አጋጣሚዎች እንዲያገኙ እንደሚረዳ አመልክቷል።

ድርጅቱ የገበያ ችግር ያለበት ቢሆንም ግን በድንጋይ ከሰሉ የጥራት ደረጃው የወረደ ነው ብለው የሚያስቡ አካላት እንዳሉ ጠቅሶ፣ እነዚህ አካላት ግንዛቤ እንዲያገኙ የሚያስችሉ ሥራዎች እየተሠሩ መሆናቸውንም ይገልጻል።

በቀጣይ ድርጅቱ ተጨማሪ ቅርንጫፎችን በመክፈት የድንጋይ ከሰል ሥራውን አስፋፍቶ መሥራት እንደሚፈልግ አቶ ዳዊት አስታውቆ፣ የድንጋይ ከሰል ለውጭ ገበያ ለማቅረብ እቅድ እንዳለውም ተናግሯል። ለዚህም መንግሥትም ሆነ ሌሎች የሚመለከታቸው አካላት ድጋፍ ሊያደርጉለት ይገባል ሲል አስታውቋል።



ፕሬዚዳንት ታዬ አፅቀ ሥላሴ ኤክስፖውን በጎበኙበት ወቅት

**የማዕድን ዘርፉን ለማልማት ከመንግሥት በተጨማሪ ባለሀብቶች እና ባለድርሻ አካላት እገዛ ሊያደርጉ ይገባል**

ሌላኛው የኤክስፖው ተሳታፊ ኤም ኤች ኤን ዋ ነው፤ ድርጅቱ 2014 ዓ.ም የተመሠረተ ሲሆን፤ የኢንዱስትሪ፣ የከበሩና የጌጣጌጥ ማዕድናትን ለውጭ ገበያ ያቀርባል።

የድርጅቱ መስራች አቶ ነጋሽ ይርጋ ሊትየም፣ ኮፐር፣ ማንጋኒዝ እና የመሳሰሉትን ለኢንዱስትሪ ግብዓትነት የሚውሉ ማዕድናት እንዲሁም እንደ ሩቢ፣ ኦፓል የመሳሰሉትን የከበሩና የጌጣጌጥ ማዕድናትን ለውጭ ገበያ እንደሚያቀርቡ ይገልጻሉ።

«በኤክስፖው መሳተፋችንን ለሀገር ውስጥና ለውጭ ተሳታፊዎችና ጎብኚዎችን ቀልብ በመሳብ ማዕድናትን ለማስተዋወቅ ያስችላል ሲሉ ጠቅሰው፣ ከእኛ ሥራዎች ጋር በተገናኘ ከሚያስፈልጉ የሀገር ውስጥም ሆኑ የውጭ ጎብኚዎች ጋር ጥብቅ ግንኙነት እንዲኖረን ይጠቅማል» ብለዋል።

እሳቸው እንደሚሉት፤ እነዚህ ማዕድናት በሀገሪቷ በተለያዩ አካባቢዎች የሚገኙ ናቸው። ሊትየም፣ ኮፐር እና ማንጋኒዝ ብዙ ጊዜ በአፋር እና በኦሮሚያ ክልል ጉጂ አካባቢ ይገኛሉ። እንደ ሩቢና ኦፓል ያሉት የጌጣጌጥና የከበሩ ማዕድናት ደግሞ ከአማራ ክልል ውሎ አካባቢ የሚገኙ ሲሆን፤ ፍሎራየትን የመሳሰሉት ማዕድናት ደግሞ ከሶማሌ ክልል እንደሚገኙ አስታውቀዋል።

ድርጅቱ ማዕድናቱን ወደ ተለያዩ ሀገራት በመላክ የገበያ መዳረሻዎች እያሰፋ መሆኑን ገልጸው፤ የከበሩ ማዕድናት አውሮፓ፣ ቱርክ፣ ዱባይ፣ ጀርመንና ሲዊዲን እንደሚላክ ተናግረዋል። እንደ ሊትየም እና ኮፐር ያሉትን የኢንዱስትሪ ማዕድናት ደግሞ ወደ ቻይናና አልፎ አልፎም አሜሪካ ገበያ እንደሚላክ አስታውቀዋል።

አሁን ድርጅቱ ከጌጣጌጥ ማዕድናት ውጭ ያሉትን አብዛኛዎቹን ማዕድናት እሴት ሳይጨመርባቸው በጥሬው እንዳለ እንደሚልክ ጠቅሰው፤ የጌጣጌጥ ማዕድናትን ከአምራቾች ተረክቦ ፕሮሰስ በሚያደርጉ አካላት በማሠራት ለገበያ እንደሚያቀርብ ይገልጻሉ። ወደፊት እሴት ጨምራ ሥራውን በራሱ ለማከናወን አቅዶ እንደሚሰራም ይገልጻሉ።

እሳቸው እንዳብራሩት፤ በማዕድናት ላይ እሴት ለመጨመር ቴክኖሎጂና በተለይ ማሽኑን ለማስመጣት ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ይጠይቃል። ለአብነትም ሊትየምን በሀገር ውስጥ ፕሮሰስ ለማድረግ ቢፈልግ ብዙ ካፒታልና ባለሙያ ያስፈልጋል። አሁን ማዕድን ሚኒስቴር በተለይ በሀገር ውስጥ መመረት የሚችሉ ማዕድናትን ለማምረት እንዲቻል የሚያደርግ ምቹ ሁኔታ ላይ ትኩረት ሰጥቶ እየሠራ ነው። በተለይ ማዕድን እሴት ተጨምሮበት ወደ ውጭ ቢላክ ዋጋው አሁን ከሚሸጠው አራትና አምስት እጥፍ እንዲሆን ያደርገዋል።

ማዕድናቱን የሚገዙት ሀገራት ስለማዕድናቱ ያላቸው ግንዛቤ በጣም ከፍተኛ በመሆኑ ጥራት ያላቸው ማዕድናት እንዲቀርቡላቸው ይፈልጋሉ። ጥራት ያለው ማዕድን ከቀረበ ገዢዎቹ ደስ ብሎቸው ስለሚገዙ በዚያ ልክ ለአቅራቢዎቹ ገበያው ጥሩ ይሆናል።

ድርጅቱ አሁን ለአምስት ሰዎች የሥራ እድል መፍጠሩን ጠቅሰው፣ ዘርፉ በስፋት ሊሰራበት የሚችል ገና ያልተነካ በመሆኑ ብዙ ሰዎች ሊሳተፉበት የሚችሉና ለብዙዎች የሥራ እድል ሊፈጥር የሚችል ነው ብለዋል።

« በማይቴክ ኤክስፖው መሳተፋችን ምርቶቻችንን እንድናስተዋወቅና የገበያ ትስስር እንድንፈጥር ረድቶናል። ብዙ ደንበኞችን እና አጋር ድርጅቶች እንድናፈራ እድል ፈጥሮልናል» ሲሉም ገልጸዋል። ድርጅቱ በቀጣይ በማዕድናት ላይ እሴት በመጨመር ለውጭ ገበያ ለማቅረብ ትኩረት አድርጎ እንደሚሰራ ጠቁመው፣ አቅሙን እያጠናከረ ራሱንም ሀገሩንም ለመጥቀም እንደሚሰራ አስታውቀዋል።

«ሙዚየም ጂም ስቶን ትሬዲንግ» ሌላኛው የማዕድን ኤክስፖው ተሳታፊ ነው። የድርጅቱ የሽያጭ ባለሙያ ወጣት ራህመት ታጁ አብደላ እንደምትለው፤ ድርጅቱ በርካታ ዓይነት የከበሩ ማዕድናት በማምረት ለውጭ ገበያ ያቀርባል። እነዚህን ማዕድናት ለተለያዩ ጌጣጌጥነት እንዲውሉ አድርጎ ይሰራቸዋል።

በጃስበር፣ ኦቮሲዲያን፣ አሜቴስት፣ አጌት እና የመሳሰሉት ማዕድናት ላይ እሴት በመጨመር ለውጭ ገበያ ያቀርባል። እነዚህ ማዕድናት በወርቅና በብር ተደርገው ለጆሮ፣ ለአንገትና ለእጅ ጌጣጌጥነት እንዲያገለግሉ ሆነው ይሰራሉ። ለልብስና ለቤት ጌጣጌጥነት በሚውል መልኩ የሚሠሩ ናቸው። ማዕድናቱ በጌጣጌጥ መልኩ ከተሠሩ በኋላ ወደ ህንድ፣ ቻይና ሌሎች የኤሽያ ሀገራት ገበያ ይላካሉ።

በማዕድናት ላይ እሴት በመጨመር በጌጣጌጥነት መልኩ ሰርቶ ለውጭ ገበያ ማቅረብ ከግለሰብ አልፎ ሀገር የሚጠቅምና የሚበረታታ ሥራ ነው የምትለው ወጣት ራህመት፤ የከበሩና የጌጣጌጥ ማዕድናት በተለያየ መልኩ በሕገ ወጥ መንገድ ከሀገር እንዲወጡ የሚደረግበት ሁኔታ የውጭ ገበያውን ሳይቀር እንዲቀዘቅዝ እያደረገ መሆኑን ጠቁማለች። በተለይ ሕገ ወጥነትን መከላከል ላይ ትኩረት ሰጥቶ በመሥራት ግንዛቤ ማስፋት እንደሚያስፈልግ ጠቁማለች።

የከበሩ ማዕድናት በሀገሪቱ በተለያዩ አካባቢዎች በስፋት እንደሚገኙ አስታውቆ፣ የአቅርቦት ችግር እንደማያጋጥም ገልጻለች፤ በአንዳንድ አካባቢዎች የሚታየው ጸጥታና አለመረጋጋት በሥራው ላይ እንቅፋት መፍጠሩን ጠቁማለች።

እነዚህን ምርቶች ለማስተዋወቅ የተለያዩ ፕላትፎርሞች እንደሚጠቀሙ ጠቅሳ፣ በኦንላይን ገበያ እንደሚሸጡ ራህመት ገልጻለች፤ ገበያ ማግኘት ዋነኛ ችግር እንደሆነ አመልክታ፣ ገበያው ሲገኝ የምርት እጥረት እንደሚያጋጥምም ነው ያስታወቀችው። ሥራው እነዚህ ላይ በደንብ መሥራት እንደሚጠይቅም ጠቁማለች።

ወጣት ራህመት እንዳለችው፤ ኤክስፖው በርካታ የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገሮች ጎብኚዎች ስለሚያሳተፍ ድርጅቱ ምርቶቹን ለማስተዋወቅና ለመሸጥ እንዲሁም ገበያ ለማፈላለግ ጥሩ አጋጣሚን ይፈጥራል። ድርጅቱ በመድረኩ ሲሳተፍ ለሦስተኛ ጊዜ ነው፤ የመጀመሪያው ዓመት መድረክ በጣም የደመቀ እንደነበር አስታውሳ፣ ብዙ ራሳችንን ያስተዋወቅንበት ነበር ብላለች። ሁለተኛውና የአሁኑ ኤክስፖው ቀዝቀዝ ያሉ መሆናቸውን አስታውቃለች። ይህ ሦስተኛው ኤክስፖ ካለፉት ኤክስፖዎች አኳያ ሲታይ የጎብኚዎች ቁጥር በእጅጉ ዝቅተኛ መሆኑንም አመልክታለች።

ህብረተሰቡ በማዕድናት ዙሪያ ያለው ግንዛቤ ለውጥ ያለው ቢሆንም አሁን የሚቀሩ ብዙ ሥራዎች አሉ የምትለው ራህመት፤ በተለይ ከሌሎቹ ማዕድናት አንጻር ሲታይ የከበሩና የጌጣጌጥ ማዕድናት ላይ እየተሠራ ያለው ሥራ የተዳከመ መሆኑን ትገልጻለች። ለአብነት የኢንዱስትሪ ማዕድናት ብንመለከት በከፍተኛ ሁኔታ ተፈላጊነት ተሰጥቷቸው እንደሚሰራባቸው ሁሉ እነዚህ ማዕድናት ላይ ትኩረት ተደርጎ ሊሰራ ይገባል ስትል አስገንዝባለች።

ወጣት ራህመት እንደምትለው፤ በከበሩና በጌጣጌጥ ማዕድናት ላይ እሴት ተጨምሮ ወደ ውጭ ገበያ ሲላኩ በጥሬው ከሚላኩት 50 እና 60 በመቶ ያህል የዋጋ ጭማሪ ይኖራቸዋል፤ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ሊያስገኙ ይችላሉ። እነዚህ ማዕድናት በኢትዮጵያ እንደሚገኙ ብዙ ሰዎች አያውቁም፤ በዚህ የተነሳም አይጠቀሙባቸውም።

ማዕድናት ሲባል የሚታወቁት ወርቅና ብር ብቻ ናቸው። የከበሩ ማዕድናት እንደ ድንጋይ እንጂ እንደ ማዕድን አይታዩም። በመሆኑም በህብረተሰቡ ዘንድ ግንዛቤ መፍጠር ላይ በማስፋት መሥራት ያስፈልጋል። «ማዕድናቱን ለውጭ ገበያ ሲናቀርብ ከወርቅ በላይ ዋጋ ሊያወጡ ይችላሉ፤ ሀገር ለገበያ ሲቀርቡ ግን ከዚህ ባነሰ ዋጋ ነው የሚሸጡት። ይህንን የምናደርገው ህብረተሰቡ የራሱን ምርቶች እንዲጠቀም ለማድረግ ነው» በማለት ታብራራለች።

ሌላኛው ተሳታፊ «ካውሰር የከበሩ ማዕድናት ኤክስፖርትና ኤምፖርት» የተሰኘው ድርጅት ነው። ድርጅቱ የከበሩና የጌጣጌጥ ማዕድናትን እንዲሁም የኢንዱስትሪ ማዕድናትን ለውጭ ገበያ ያቀርባል። እንደ ኦፓል፣ ሳፋየር እና ኤምራልድ ያሉ የከበሩና የጌጣጌጥ ማዕድናትን በኦንላየን ገበያ ይሸጣል። :

የድርጅቱ የሽያጭ ባለሙያ ሁዳ አብዳል ፈታ እንደምትለው፤ ድርጅቱ ከኢንዱስትሪ ማዕድናት መካከል እንደ ታንታለየም፣ የድንጋይ ከሰል የመሳሰሉትን ለተለያዩ ፋብሪካዎች ያቀርባል። እነዚህን ማዕድናት ከተለያዩ አምራቾች ተረክቦ ለፋብሪካዎች ያቀርባል።

ሌላው ለሜካፕ መሥሪያ የሚያገለግለው ማይካ፣ የተሰኘው ማዕድን ነው፤ ማዕድኑ ሜካፕ ለሚሰሩ ፋብሪዎች ይቀርባል። ለሀውልቶች ሥራ የሚያገለግለው ኮሪስታል ኦፓልንም እንዲሁ ያቀርባል። አምበር የተሰኘ ለተለያዩ ጌጣጌጥ መሥሪያ የሚያገለግለው ማዕድን አቅራቢም ነው።

ድርጅቱ በኤክስፖ ላይ መገኘቱ እነዚህን ምርቶች ለማስተዋወቅና የገበያ ትስስር ለመፍጠር እንዳስቻለው ጠቅሳ፣ ኤክስፖው ምርቶችን ለመሸጥ፣ በርካታ የውጭና የሀገር ውስጥ ደንበኞች ለማፍራት አስችሎናል ስትል ትገልጻለች።

መዝናኛ

# የብዕር ጠብታ

## የእግዜር ቀጠሮ

ከእግዜርጋ ቀጠሮ ያዝን። ቦታውም የዕድሜ አውቶቡስ በምታልፍበት ፌርማታ ላይ። ሰዓቴን ሳላዛንፍ እንዲያውም አንድ አስር ደቂቃ ቀደም ብዬ ተገኘሁ። ፈንጠር ብሎ አንድ ሽማግሌ ዓይነ ስውር ነዳይ ምጽዋት ይለምናሉ።

ገና ከመድረሴ ነዳዩ፦ "የኔ ልጅ ተዘከረኝ ቀኑ የጨለመብኝ ሌቱ ..." አላስጨረስኳቸውም "እግዜር ይስጥልኝ አባቴ"

ስንገናኝ ምን እደንምለው ምን እንደምጠይቀው ምን እንደምወቅሰው እያሰላሰልኩ ጥበቃዬን ተያያዝኩ።

የዕድሜ አውቶቡስ ዝም ብሎ ያልፋል።

"የሚመራኝ ልጅ ጠዋት እዚህች ድንጋይ ላይ የኀለተኝ ነኝ። ምን ሆኖ እንደሁ አላውቅም ያለውትሮው ዘገየብኝ። ከነጋ እህል ባፌ አልዞረም" አሉ ለማኙ

አልመለስኩላቸውም።

"አንዳች የሚበላ ነገር ይዘህ ይሆን?"

"አባቴ ይቀልዳሉ ልበል?"

"አትበል። ቀልዴን አይደለም። "

"ሲያዩኝ ርዳታ ማስተባበሪያ መስላለሁ እንዴ?"

"ይቅርታ ልጄ አትቆጣ። እንዲያው አፍ የሚያካፍት ስላገኘሁ ደስ ብሎኝ ነው። ዓይኔ ታወረ እንጂ ልሳኔ አልተዘጋም። ለምን እንደሁ እንጃ ግን ሰው አያወራኝም። " ያዘኑ መሰሉ።

እኔ ምናገባኝ ታዲያ አልኩ በሆዴ።

"አንዱ ስላንዱ ማሰብ ተው። ፍቅር ቀዘቀች። ለምን ይመስልሃል ልጄ?"

"እንጃ!"

"ምክንያቱም ስግብግቦች ስለሆንን ነው። ሆዳሞች ስለሆንን ነው። "

ሰዓቴን አስር ጊዜ አያለሁ።

ምነው እግዜር አረፈደ?። . . .

የዕድሜ አውቶቡስ ዝም ብሎ ያልፋል።

"ግን የአምላክ ዓላማ እንዲያ አልነበረም። " አሉ አዛውንቱ "የሱማ ዓላማ ፍቅር ነበር። እርስ በርሳችን ስንዋደድ ነው መንግሥቱን የምናሰፋ። እኛ ግን እርስ በርስ ጦር እንሳበቃለን። ሠይፍ እንማዘዛለን። ለጊዜያዊ ጎጆችን ዘላለማዊ ቤታችንን እናፈርሳለን። "

ትግስቴ አለቀ። ከዚህ በላይ መጠበቅ አልቻልኩም። ግን ቆይ ምናልባት እግዜር እንደ አበሻ ሊሆን ስለሚችል ትንሽ ልጠብቀው።

የዕድሜ አውቶቡስ ዝም ብሎ ያልፋል።

"ምን እየጠበክ ነው ታዲያ?" አሉ ሽማግሌው።

"መቼም አባቴ አንድ ሰው ፌርማታ ከተገኘ አውቶቡስ እንጂ ዶሮ አይጠብቅ"

ፈገግ አሉ። ድምጻቸውን እንደመሞረድ አረጉና "ሰማህ ልጄ" አሉ "ሰማህ የዕድሜ አውቶቡስ በፌርማታ ሲያልፍ እንጂ መቼ ሲቆም ታይቶ ያውቃል?"

"ታዲያ ፌርማታ ለምን ተሠራ?"

"እግዜርን መጠበቂያ ነዋ። እግዜርና ሰው ቀጠሮ የሚይዙት ከእድሜ አውቶቡስ ፌርማታ ነው። አንተም ከእግዜርጋ ቀጠሮ ይዘህ የመጣህ መስሎኝ"

"ልክ ነዎት። ግን እንዴት አወቁ?"

"ብዙ ሰው እንዳንተ ከግዜርጋ ቀጠሮ አለኝ እያለ በየጊዜው ይመጣል። እኔ ደሞ ሽቀላዬን እዚቹ ፌርማታ ስር ተቀምጬ ስለሆነ ምሽቅለው በዚህ አውቃለሁ"

"ታዲያ እንደተቃጠሩት እግዜር በሰዓቱ ይመጣላቸዋል?"

"አዎ። ግን ብዙዎቹ ትተውት ይሄዳሉ። "

"እንዴት?"

"አላውቅም። ይቀጥሩትና በሰዓቱ ሲመጣላቸው ትተውት ይሄዳሉ"

"ታዲያ ለኔ ለምን በሰዓቱ አልመጣልኝም? . . . ይሄው አሁን እንኳ ግማሽ ሰዓት አለፈው"

ሽማግሌው ፈገግ አሉ።

"እኮ የታል እግዜር?"

"እንግዲህ እኔ ዓይን የለኝ እንዳላፋልግህ። ዞር ዞር እያልክ ፈልገዋ ልጄ"

የዕድሜ አውቶቡስ ዝም ብሎ ያልፋል።

እንዳሉኝ ወደ ግራም ወደ ቀኝም ዞር ዞር እያልኩ እግዜርን ፈለኩት። ባካባቢው ከኔና ከዓይነሥውሩ ለማኝ በቀር ማንም የለም።

ወደ ቤት ልመለስ ተነሳሁ።

"በቃ ተስፋ ቆርጠህ ልትሄድ ነው?" አሉ ነዳዩ

"ምንም ማድረግ አልችልም። ከዚህ በላይ የምጠብቅበት ትግስት የለኝም። ከመጣ ግን ጠብቄው ጠብቄው ጠብቄው . . . ተስፋ ቆርጬ እንደሄድኩ ይንገሩልኝ"

እቤት ስደርስ ስልኬ አቃጨለ። እግዜር ነው።

"ምነው? ምናረኩህ? ምንበደልኩህ? ምን አስቀየምኩህ? ምን አጠፋሁ እግዜር?"

"ምን ሆነሃል?"

"ጭራሽ ምንሆነሃል? ትለኛለህ?! . . . አንድ ሰዓት ሙሉ አስደግፈኸኝ?"

"አላስደገፍኩህም። ቀድሜህ ነው የተገኘሁት። አንድ ሰዓት ብቻ ሳይሆን ዕድሜ ልክ ነበር የጠበኩህ። እጠብቅሃለሁም። "

"ጭራሽ ቀድሜህ ትለኛለህ? ጭራሽ ዕድሜ ልክ ጠበኩህ ትለኛለህ?. . . አንተም እንደሰው ትቀልዳለህ እንዴ እግዜር?"

"እረ በፍጹም። "

"ታዲያ በቀጠሯችን ቦታ መች ተገኘህ?"

"እዚያው ነበርኩኮ። ስላልፈለከኝ ነው። "

"እኮ የቷ? . . . አስታውሳለሁ አጠገቤ ከነበሩት ዓይነስውር ለማኝ በቀር በስፍራው ማንም አልነበረም"

"ታዲያ ዓይነ ስውሩ ለማኝ እኔ አልነበርኩ እንዴ?"

"ምናልክ?"

"ሰምተሃል። "

***

**(ከዳዊት ወርቁ አጫጭር የልቦለድ ስብስቦች የተወሰደ)**

# ዓለም አቀፍ

## በመካከለኛው ምስራቅ የፈነጠቀው የሰላም አየር

**ቦጋለ አበበ**




አስራ አራት ወራት ለተጠጋ ጊዜ የተወረወሩ ድምበር ዘለል የጦር ፍላፃዎች በሺዎች ለሚቆጠሩ ንፁሃን ሞትና መፈናቀል ምክንያት ሆነዋል። ለከፉ ጥቃቶች፣ ለበርካታ ወታደሮችና ቁልፍ ወታደራዊ መሪዎች ሞት መንስዔ የሆኑ የጥይት አረሮች ካለፈው ማክሰኞ ምሽት ጀምሮ ወደ ሰገባቸው ተመልሰው ሰላም እንደ ውሃ ለጠማው ሕዝብ ለጊዜውም ቢሆን እፎይታ ሰጥተዋል። በእስራኤልና በሊባኖሱ ታጣቂ ሄዝቦላ ቡድን መካከል የአየርና የምድር ግጭቶች ለተወሰነ ጊዜም ቢሆን በተኩስ አቁም ስም እንዲገቱ ስምምነት ላይ ተደርሷል። ይህ እለት ከእለት ነብሳቸውን በጨርቅ መጠቅለል ለቀራቸው ንፁሃን ትልቅ ብስራት ነው። የተኩስ አቁም ስምምነቱ በተለይም ለሰሜን እስራኤልና ደቡብ ሊባኖስ ዜጎች ትልቅ ትርጉም አለው ተብሏል።

ተሰናባቹ የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ጆ ባይደን ያቀረቡት ምክረ ሃሳብ በሁለቱም ወገኖች ተቀባይነት ማግኘቱ በብዙዎች ዘንድ እውን ለስልሳ ቀናት የታወጀው የተኩስ አቁም ስምምነት ወደ ዘላቂ ሰላም ለማምራት ያበቃ ይሆን? የሚል ጥያቄ አጭሯል። ፕሬዚዳንት ባይደን ማክሰኞ ምሽት ስለተኩስ አቁም ስምምነቱ በሰጡት መግለጫ፣ "በሊባኖስና በእስራኤል መካከል ሲካሄድ የቆየው ድምበር ዘለል ጦርነት ማብቂያው ይሆናል፣ ያቀረብነው የተኩስ አቁም ስምምነትም ለዘለቄታው ጦርነቱን ለማስቆም ከግምት ያስገባ ነው" ብለዋል።

በሁለቱም ወገኖች ያሉት ሲቪል ማህበረሰቦች በቅርቡ ወደ ህብረተሰባቸው በሰላም ተመልሰው መደበኛ ሕይወታቸውን ይመራሉ ሲሉም ባይደን ተናግረዋል። የሞት ሱናሚ ሲንጠው የቆየው የሊባኖስ ሰማይ የሰላም አየር ይነፍስበት ዘንድ በፕሬዚዳንት ባይደን የቀረበው ሃሳብ በሊባኖሱ ጊዜያዊ ጠቅላይ ሚኒስትር ናጂብ ኒካቲ በኩል ተቀባይነት ለማግኘት አፍታ አልፈጀበትም። ኒካቲ የተኩስ አቁም ስምምነቱን በደስታ እንደሚቀበሉ ለፕሬዚዳንት ባይደንም አሳውቀዋል።

ከጦር እስከ ረሃብን እንደ ጦር መሣሪያ የመጠቀም ወንጀል ዓለም አቀፉ የወንጀለኞች ፍርድ ቤት የእስር ማዘዣ ያወጣባቸው የእስራኤሉ ጠቅላይ ሚኒስትር ቤኒያሚን ኔታኒያሁ፣ ለአሜሪካው ፕሬዚዳንት መንግሥታቸው የተኩስ አቁም ስምምነቱን ማፅደቁንና ባይደንም እስራኤል ራሷን የመከላከል መብት እንዳላት መጥቀሳቸውን በማድነቅ ለስምምነቱ ተገዢ መሆናቸውን ገልፀዋል። «ሄዝቦላህ ስምምነቱን ጥሶ ራሱን ለማስታጠቅ የሚሞክር ከሆነ ግን ጥቃት እንፈፅማለን፣ በድንበር አካባቢ የሽብር መሠረተ ልማት የሚገነባ ከሆነም እናጠቃለን» ያሉት ኔታኒያሁ፣ እስራኤል በሰሜናዊው ጎረቤቷ ከሚንቀሳቀሰው ሄዝቦላህ ጋር ስምምነት መፍጠሯ የእስራኤል ጦር ትኩረቱን ኢራን ላይ ብቻ ለማድረግ እንደሚያስችለውም ተናግረዋል።

አሜሪካ ባቀረበችው በዚህ የተኩስ አቁም ስምምነት ዝርዝር ነጥብ መሠረት እስራኤል በሚቀጥሉት ስልሳ ቀናት ጦሯን ከደቡብ ሊባኖስ በሂደት የምታስወጣ ሲሆን፣ በምትኩም የሊባኖስ ጦርና የመንግሥት የፀጥታ ሃይሎች ወደ ግዛቱ የሚሠማሩ ይሆናል። ባይደን ከፈረንሳዩ ፕሬዚዳንት ኢማኑዔል ማክሮን ጋር ባወጡት መግለጫ ሁለቱ ሀገራት ስምምነቱ ሙሉ በሙሉ መተግበሩንና ተፈፃሚ መሆኑን ለማረጋገጥ ከእስራኤልና ሊባኖስ ጋር እንደሚሠሩ በአፅኖት ገልፀዋል። በተጨማሪም አሜሪካና ፈረንሳይ የሊባኖስን መንግሥት የጦር ሃይል ለመገንባትና በመላው ሊባኖስ ውስጥ መረጋጋት ተፈጥሮ ሀገሪቱ ወደ ልማት ፊቷን እንድታዞር የሚደረጉ ዓለም አቀፍ ጥረቶችና ድጋፎችን ከፊት ሆነው ለመምራት ቃል ገብተዋል።

ሀማስ እስራኤል ላይ ከዓመት በፊት የፈፀመውን ጥቃት ተከትሎ እስራኤል ከወሰደችው ምላሽ ማግስት ሄዜቦላ ከሀማስ ጎን በመቆም ነበር አዲስ የጦርነት ምዕራፍ የከፈተው። በዚህም ምክንያት በሄዝቦላና እስራኤል መካከል በርካታ የሚሳዔልና የሮኬት ጥቃቶች ሲፈፀሙ ቆይተዋል። ነገሩ እየተባባሰ ሲሄድ እስራኤል ከወር በፊት እግረኛ ወታደሮቿን በደቡብ ሊባኖስ አሰማርታ ርምጃ መውሰድ መጀመሯ ይታወቃል። ይህም ከሶስት ሺ በላይ ሊባኖሳውያን ሕይወታቸውን እንዲያጡ ከማድረጉ በተጨማሪ ከአስራ አምስት ሺህ በላይ የሚሆኑ መቁሰላቸውን መረጃዎች ያመለክታሉ።

ጦርነቱ በሊባኖስ ካስከተለው ሠብዓዊ ቀውስ ባሻገር ኢኮኖሚያዊ ኪሳራም ያደረሰ ነበር። እንደ ዓለም ባንክ መረጃ በዚህ ጦርነት ምክንያት የ8 ነጥብ 5 ቢሊዮን ዶላር የኢኮኖሚ ኪሳራ ደርሷል። የወደሙ መሠረተ ልማቶችን መልሶ ለማቋቋምም ረጅም ጊዜ የሚፈጅ ሲሆን፣ በማን ወጪ ይሸፈናል? የሚለው ጉዳይ ሌላ ጥያቄ የፈጠረ ሆኗል።

በሰላም ስምምነቱ መሠረት የእስራኤል ጦርና የሄዝቦላ ተዋጊዎች ከያዟቸውን የደቡባዊ ሊባኖስ ቦታዎች ከወጡ በኋላ በሺዎች የሚቆጠሩ የሊባኖስ ወታደሮች እንደሚሠማሩ ይጠበቃል። ይህ እንዴት ተፈፃሚ ይሆናል? የሚለው ጉዳይ ግን በግልፅ አልተቀመጠም። የሊባኖስ ወታደሮች የተሰጣቸውን ግዳጅ ለመወጣትም የሚያስችል ሀብት ወይም በቂ ገንዘብ፣ የሰው ኃይልና የመሣሪያ አቅም የላቸውም በማለት የሀገሪቱ መንግሥት ለዓለም አቀፉ ማህበረሰብ የድጋፍ ጥያቄ አቅርቧል። በጉዳዩ ላይ አስተያየት የሰጡ አንዳንድ ተንታኞች የገንዘብ ድጋፉ ከተለያዩ የሊባኖስ ዓለም አቀፍ አጋሮች ሊገኝ ይችላል የሚል ተስፋ አላቸው። መሣሪያና ተጨማሪ የሰው ሃይል ማሠልጠን የተፈለገው ግን በሊባኖስ መንግሥት በኩል ሂዝቦላን እስከወዲያኛው ለማዳከም ታስቦ ሊሆን ይችላል ይላሉ። ይህም በቀጣዮቹ ጊዜያት የሊባኖስ ጦር ከሂዝቦላ ጋር ወደ ሌላ የግጭት ምዕራፍ እንዳይገባ ስጋታቸውን ያጋራሉ።

የተኩስ አቁም ስምምነቱ ከእስራኤል ጋር ያለውን ግጭት ወደ ፍፃሜ ሊያመጣ ይችላል የሚለው እምነት የበርካቶች ሆኗል።

በሥልጣናቸው የመጨረሻ ወራት ላይ እስራኤልና ሄዝቦላን ወደ ተኩስ አቁም ድርድር ማምጣት የተሳካላቸው ፕሬዚዳንት ባይደን በቀረቻቸው ጥቂት የሥልጣን እድሜ ከቱርክ፣ ግብፅ፣ ካታር፣ እስራኤልና ከሌሎችም ጋር ንግግር በማድረግ በጋዛ ተኩስ አቁም ተግባራዊ እንዲሆን ለማድረግ ቃል ገብተዋል። በተጨማሪም በጋዛ ጦርነት ምክንያት ወደ ኋላ የተመለሰውን ሳውዲ አረቢያን ጨምሮ በእስራኤልና በሌሎች የአረብ መንግሥታት መካከል ተጀምሮ የነበረውን በጎ የግንኙነት ምዕራፍ በማደስ አዳዲስ ስምምነቶችን ለማበጀት እንደሚሠሩም ቃል ገብተዋል።

ማህበራዊ

# ሀገርኛ

# የዓመቱ መድኃኒት የሚሰበሰብበት - ሳሞ-ኤታ

**ቤዛ እሸቱ**



**አረንጓዴ የለበሰውና የዓመቱ መድኃኒት የሚለቀምበት የቦር ተራራ**

ሀገር የትውልዶች ቅብብሎሽ ውጤት ናት። በዚህ መሃል መወለድ ማደግ መታመም መሞት ቢኖርም የተወለደው የሞተውን እየተካ ሕይወት ቀጥሏል። በዚህ ሂደትም ቅጠል በጥሶ የዳነ፤ ዳማከሴን አሻሽቶ የተፈወሰ ጥቂት አይደለም። በማናውቃቸው ባሕላዊ መድኃኒቶች ፈውስን ያገኙም በርካታ ናቸው። ለዚህም ቀደምቶቻችን ሊመሰገኑ ይገባል። በእነርሱ ጥረት ሕመሞች ተለይተው ታውቀዋል። በሽታዎች መፍትሔ አግኝተዋል። ሲማቅቁ የነበሩ ሰዎች ቀና ብለው እንዲሄዱ ሆነዋል። ሕይወታቸውን ሊያጡ የነበሩም አዲስ ሕይወታቸውን ቀጥለዋል። ለዚህም ነው ባሕላዊ መድኃኒቶቻችን ዛሬ ድረስ በትውልድ ቅብብሎሽ እዚህ ላይ የደረሱት።

በሀገራችን የባሕል መድኃኒትን ለትውልድ በማስተላለፍ የሚታወቁ ሕዝቦች አሉ። ዛሬ በምናባችን የምንጓዘው በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ከሚገኘው የም ዞን ነው። የዞኑ ዋና ከተማ የሆነችው ሳጃ ከአዲስ አበባ በ239 ኪሎ ሜትር ርቀት ከክልሉ ዋና ከተማ ሆሳዕና በ221 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ትገኛለች።

የየም ማህበረሰቡ ከእጽዋት ጋር ጥብቅ ቁርኝት አለው። አብዛኛው ማህበረሰብ በግብርና የሚተዳደር ሲሆን፤ በተለይ እንሰት የኑሮው መሠረት ነው። ከእንሰት ዎቶ፣ ናቱ፣ ዳኣ፣ ባራሳ(ባራሲኛ)፣ ኡዋ፣ ኬራ፣ እርካ የተሰኙ ጣፋጭ ምግቦቹን አዘጋጅቶ ይመገባል። ሾሮዶ (ባሕላዊ የልብስ ሳጥን)፣ ኦፖ(ጂባ)፣ ጋዱ(ገመድ) የተሰኙ የቤት መገልገያዎችን ከእንሰት አዘጋጅቶ ለቤት ፍጆታ ያውላል። በተመሳሳይ እነዚህን ሥራዎቹን ሸጦ ከሚያገኘው ገቢ ይጠቀማል።

የየም ሕዝብ ከእጽዋት ጋር ያለውን ቁርኝት የዞኑን መልክዓ ምድር ያየ ሰው ይገምታል። አካባቢው በአረንጓዴ እጽዋት ያጌጠ ነው። በተለይ ከባሕር ጠለል 2939 ሜትር ከፍታ ላይ የሚገኘው የቦር ተራራ ሙሉ አረንጓዴ ለብሶ መመልከት ለዓይን ከመማረኩም በላይ የአዕምሮን ሰላም ያድሳል።

ለየም ሕዝብ ጥቅምት 17 ልዩ ቀን ነው። ስለዚህም አረንጓዴ ከለበሰው ቦር ተራራ ያለ ቀጠሮ ይገናኛል። ከአባቶቹ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ የመድኃኒት ቀለቡን በነፃ ሊሸምት በማለዳ ከተራራው ይከትማል። በዕለቱ ቁርስ ስጡኝ፤ ስንቅ አዘጋጁልኝ ሳይሉ ሁሉም ፀሐይን ቀድመው ከተራራው አናት ላይ ይከትማሉ።

የዞኑ ባሕል እና ቱሪዝም መምሪያ ኃላፊ አቶ መስፍን ሞጋ እንደሚሉት፤ የየም ማህበረሰብ ከተፈጥሮ እጽዋት መድኃኒት ለቅሞ በመቀመም ሕይወትን ታድጎ የቆዩ ነው። በአካባቢው ጤንነትን ጠብቆ የሚኖር ስለሆነም ምድሩን የፈውስ ምድር እስከ ማለት ይደርሳል። ለዚህ ደግሞ ጥቅምት 17 በቦር ተራራ ላይ የሚበቅሉ እጽዋት እና አበቦች ምስክር ይሆናሉ። እነዚህ እጽዋት ምድሪቱን ሞልተው ለሕዝቡ ጥንካሬን ያላብሳሉ፤ እስትንፋስንም ይመልሳሉ። በመሆኑም ጥቅምት 17ን "አጋማሽ ወር" በመሆኑ እና ከዚህ ወቅት ካለፈ ደግሞ የሚደርቁ በመሆኑ ዕለቱ ተመርጦ የመድኃኒት መሰብሰቢያ ቀን እንዲደረግ ሆኗል።

በየዓመቱ የመድኃኒት እጽዋት የሚለቀምበት 2939 ሜትር የሚረዝመው ቦር ተራራ ሲሆን፤ በዞኑ ከፍ ብሎ የሚታይ ቦታ ነው። የመጀመሪያውን የማለዳ የፀሐይ ብርሃን ቀድሞ የሚያገኝ መሆኑ ደግሞ ተመራጭ አድርጎታል። ቦታው ላይ የሚገኘው እፅዋት የበሽታ መከላከልና ፈዋሽነት አቅም ከፍተኛ እንደሆነም ይታመናል። የሞች ፈጣሪ ፈቅዶ በሰላምና በጤና ለጥቅምት 17 ከደረሱ በማለዳ መገኛቸው ቦር ተራራ ነው። የበረታው በእግሩ፣ ካልሆነም ባገኘው የመጓጓዣ አማራጭ በቡድንም ሆነ በተናጠል ሳይታመም ከመድኃኒቱ ሊገናኝ ይጓዛል። ታሞ አልጋ ከያዘ፣ በእድሜ ምክንያት አቅም ካነሳቸው አዛውንቶች በስተቀር ማንም አይቀርም።

ዕለቱ የዓመት የመድኃኒት ስንቅ የሚሰበሰብበት ነውና ለሰበሰቡት መድኃኒት መያዣ ማዳበሪያ፣ ጆንያ፣ ላስቲክና ሌሎች የሰበሰቡትን ሊይዙ የሚችሉ መያዣዎችን ይዘው ከተራራው ይገኛሉ። መድኃኒት መሰብሰቡ ቅጠል ከመቁረጥ አለፍ ሲል ሥሮችን ወደ ማውጣት፣ የዛፍ ቅርፊት ወደ መሰብሰብና ቅርንጫፎች ወደ መቁረጥ ይሻገራል። ስለዚህም መቆፈሪያና መቁረጫዎችም የያዙ የተሻለ ሰብሳቢ ይሆናሉ።

ዓመታዊ የመድኃኒት ለቀማ ትዕይንቱ ማራኪና ለየት ያለ ባሕላዊ እውቀት የሚንፀባረቅበት ነው የሚሉት የቢሮ ኃላፊው፤ መድኃኒቱ የሚለቀመው ከተለያዩ የዛፍ፣ የሣር እና የሀረግ ዓይነቶች መሆኑን ይናገራሉ። በቦር ተራራ ላይ የደረሰው ሁሉ ያለ ምንም ከልካይና ጠያቂ ከተከለከለው እጽዋት ውጭ ያሉትንና ይጠቅሙኛል ያላቸውን ለይቶ መልቀም ይችላል። መድኃኒት ሰብሳቢዎቹ የዛፍና የሣር ዝርያዎችን ቅጠሉን ቅርፊቱንና ሥሩን መልቀም ይጀምራሉ። በዕለቱ ሕብረተሰቡ ለዓመት የሚጠቅመውን መድኃኒት የሚሰበስብ ይሰበስባል።

የሞች የሚሰበስቡት መድኃኒት ለሰው ብቻ ሳይሆን ለእንስሳትም ያገለግላል። እንስሳቱም የእነሱ አካል ናቸውና እነርሱን ማከሚያ ብልሀቱን ከነመድኃኒቱ ከአባቶቻቸው ወርሰዋል። በቦር ተራራ ላይ የተለመዱ እስከ 210 ዝርያዎች ያሉት እጽዋት መኖሩን የሚገልጹት አቶ መስፍን፤ ከእዚህ ውስጥ የ106 እጽዋት ጥቅማቸው ተለይቶ መታወቁንና ለመድኃኒትነት የሚያገለግሉ መሆናቸውን ያስረዳሉ። መድኃኒቱ በአካባቢው ማህበረሰብ ሳሞ-ኤታ በመባል የሚታወቅ ሲሆን፤ ትርጉሙም የከረመ መድኃኒት ማለት ነው። ሳሞ-ኤታ ባሕላዊ መድኃኒት ከተለያዩ በሽታዎች የሚፈውስ በመሆኑ ሕብረተሰቡ ለዘመናዊ ህክምና የሚያወጣውን ወጪ ከመቀነሱም ባሻገር የተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎችን የሚያስተሳስር መሆኑን ይጠቁማሉ።

እንደ አቶ መስፍን ማብራሪያ፤ ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲተላለፍ የመጣውን የቦር ተራራ በፈዋሽነቱና ቦታው ላይ ብዙ እፅዋት ስለሚገኝ፤ በርካታ የመድኃኒት እጽዋት በአንድ ቦታ በማግኘት በርካታ መድኃኒት መቀመም ይቻላል በሚል እሳቤ ማሕበረሰቡ ፈዋሽ ብሎ ተስማምቶበታል። ለጤና ጠንቅ የሆነውን በሽታ ለመከላከልና ለማስወገድ ሲባል በባሕላዊ መንገድ ጤንነትን የመጠበቅ ዘዴ ከጥንት ጀምሮ ከትውልድ ትውልድ ሲተላለፍ የመጣ በመሆኑ የባሕላዊ መድኃኒት ለቀማው፣ቅመማውና ህክምናው በስፋት በብሔረሰቡ ውስጥ ሰርፆ የቆየ ሀገር በቀል ዕውቀት ነው። ዘመኑ የዘመናዊ ህክምና ተስፋፍቶበታል ተብሎ የሚታሰብበት ቢሆንም በዞኑ ባሕላዊ መድኃኒት በቀላሉ እና ነፃ በሚባል ደረጃ በመገኘቱ አሁን ድረስ ተፈላጊ ሊሆን ችሏል። የባሕል መድኃኒቱ የጎንዮሽ ጉዳት የሌለበት መሆኑን በማንሳት ሕብረተሰቡ በሰፊው ይጠቀመዋልም።

ጥቅምት 17 ሁሉም ያለ ከልካይ በቦሩ ተራራ ላይ

**የየም ሕዝቦች የሚሰበስቡት መድኃኒት ለሰው ብቻ ሳይሆን ለእንስሳትም የሚያገለግል ሲሆን፤ መድኃኒቱ በአካባቢው ማህበረሰብ ዘንድ ሳሞ-ኤታ ይባላል**

ለዓመት ይበቁኛል ብሎ የሚያስባቸውን የመድኃኒት ግልጋሎት ያላቸው ቅጠላ ቅጠሎች፣ ስራስሮች፣ ቅርፊቶች ወደ መኖሪያ ቤት ተወስደው የሚለዩ ናቸው። ከተራራው የተሰበሰበውን የመድኃኒት ዝርያ በዓይነት ማደራጀትና ወደ መድኃኒትነት መቀየር ቀናትን ይወስዳል። የሚደርቀውን ማድረቅ፣ የሚወቀጠውን መውቀጥ፣ እንደ አስፈላጊነቱም ከሌላ እጽዋት ጋር መቀላቀል የግድ ይላል። በዚህም በተቀሩት የጥቅምት ቀናት አብዛኛው ሰው በአካባቢው መድኃኒት ያዘጋጃል።

የተቀመመው መድኃኒት በንፁህ ዕቃ ተቀምጦ እስከ መጪው ዓመት ድረስ ብቻ አገልግሎት ይሰጣል። ዓመት ካለፈው በኋላ የተረፈ መድኃኒትም ካለ የአገልግሎት ጊዜው አልፏልና ይወገዳል እንጂ አገልግሎት ላይ እንደማይውል የሚናገሩት አቶ መስፍን፤ ከመድኃኒት እጽዋት ልየታው፣ እስከ ቅመማ፣ እንዲሁም አወጋገድ ድረስ ያለው ሂደት እውቀት ይፈልጋልና እውቀቱን ከወላጅ የወረሱ የዛሬ ወላጆች እነሱም በተራቸው ለትውልድ ያስተላልፋሉ ይላሉ።

በዕለቱ የመድኃኒት ለቀማው ሥርዓት በተለያዩ አካባቢዎች የሚካሔድ ቢሆንም በዋናነት የዖታ፤ የሃይማኖት፤ የዕድሜ ልዩነት ሳይኖር ሰዎች ከተለያዩ አካባቢዎች ወደ ቦር ተራራ በመውጣት ይለቅማሉ። ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ በተሠራው ባሕሉን የማስተዋወቅ ሥራ ከየሞች በተጨማሪ ጥቅምት 17 በቦር ተራራ ላይ ከፍተኛ ባለሥልጣናትና በርካታ ቱሪስቶች በመድኃኒት ለቀማው ላይ እየተሳተፉ ይገኛሉ። በዕለቱ በቦር ተራራ ላይ ከሚገኙት ሱሉቶ እና ቶቱ ከሚባሉት የእፅዋት ዓይነቶች በስተቀር ሁሉም ይለቀማል። እነዚህ እጽዋት ለጊዜው ጥናት ስላልተደረገባቸው እንጂ ለመድኃኒትነት አገልግሎት ባይውሉም መርዛማነት ያላቸው በመሆኑ ለተባይ ማጥፊያና ለሌሎች አገልግሎቶች መዋል የሚችሉ ናቸው ተብሎ እንደሚገመትም አቶ መስፍን ያስረዳሉ።

በተለያዩ ምክንያቶች በሳሞ-ኤታ ላይ ሳይሳተፍ የቀረ መድኃኒት ፈላጊ የፈለገውን መድኃኒት ቢጠይቅ የሄዱት አይከለክሉትም። በየሞች እያለ የለም ማለት አይታሰብም። ሲጀመር መድኃኒቱን ሲሰበስቡም በተለያየ ምክንያት ወደ ተራራው የማይመጡትን ታሳቢ ያደርጋሉ። ስለዚህም በየም ሕዝብ ዘንድ የሰበሰቡትን መድኃኒት ማካፈል ባሕል ነው። መጀመሪያውንም ከአቅም በላይ ምክንያት ካልገጠማቸው የሞች ከሥርዓቱ አይቀሩም።

የቢሮ ኃላፊው በማህበረሰቡ በሀገር በቀል እውቀት ከ60 በላይ ለሚሆኑ ዋና በሽታዎች ፍቱን የሚሆኑ መድኃኒቶች ተለቅመውና ተቀምመው ለሰው እና ለእንስሳት ይሰጣሉ ይላሉ። የየም ብሔረሰብ የባሕል መድኃኒት አጠቃቀም ሀገር በቀል እሴት ከሌሎች የኢትዮጵያ ክፍሎች ልዩ የሆነ እና ሕብረተሰቡ በሙሉ የሚጠቀምበትና የሚጠብቀው ነው። ባሕሉ በደንብ ቢተዋወቅ ለሀገሪቱ የቱሪስት መስህብ ከመሆን ተጨማሪ የገቢ ምንጭ መሆን የሚችል እሴት እንደሆነ ይጠቅሳሉ። የዞኑ አስተዳደር ሳሞ-ኤታን በዓለም ቅርስነት ለማስመዝገብ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ተቀናጅቶ በመንቀሳቀስ ላይ እንዳለም ያነሳሉ።

የሞች ሰውነታቸው ገብቷቸዋል። ዛሬን በጤና ቢንቀሳቀሱ የዛሬ ጤንነታቸው ለነገ ዋስትና እንደ ማይሆናቸው ተረድተዋል። ለዚህም መድኃኒታቸውን ቀድመው አዘጋጅተው መጠበቅን ምርጫቸው አድርገዋል። በትውልድ ቅብብሎሽ እዚህ የደረሰን ባሕል ማዳበር ደግሞ የዚህ ዘመን ቀጣይ የቤት ሥራ ነውና ባሕሉን እንንከባከበው።

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው:: በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም::

ፖለቲካ እና ወቅታዊ

# ነፃ ሃሳብ

# የሶማሊያ መንግሥት አሁናዊ አካሄድ አልሸባብ እንደገና እንዲያንሰራራ እድል የሚሰጥ ነው

አሲ ሴሮ

ኢትዮጵያ እና የሰላም ማስከበር ተልዕኮ ተነጣጥለው የሚታዩ አይደሉም። ሀገሪቱ በተባበሩት መንግሥታት እና በአፍሪካ ህብረት የሰላም ተልዕኮ በበርካታ ሀገራት ተሳትፋለች። ቀደም ባለው ጊዜ በኮሪያ እና በኮንጎ፤ በቅርብ ዓመታት ውስጥ በሩዋንዳ፤ በቡርንዲ፤ በላይቤሪያ፤ በሶማሊያ እና በሱዳን የሰላም አስከባሪ ኃይል አሰማርታለች። በዚህም ከሀገሪቱ አልፎ በዓለም አቀፍ ደረጃ በርካታ እውቅናዎችን አግኝታለች።

የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ይፋዊ ድረ ገጽ ላይ ያለው መረጃ እንደሚያመለክተው፤ ሀገሪቱ በተለያዩ ሀገራት ሠራዊት በመሰማራት ላደረገችው የሰላም ማስከበር ተልዕኮ እውቅና ተሰጥቷታል። ኢትዮጵያ የሕይወት መስዋዕትነትን ጭምር በመክፈል በተለያዩ ሀገራት ውጤታማ የሰላም ማስከበር ተልዕኮ ማከናወኗን፤ ሰላም የሰፈነባት ዓለም ለመፍጠር የሚደረገውን ጥረት በማገዝ ከፍተኛ ሚና መጫወቷን በአድናቆት ይገልጻል።

የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት በተሰማራበት የሰላም ማስከበር ተልዕኮ ፤ ወታደራዊ ዲስፕሊንና ሙያዊ ደረጃውን በጠበቀ መልኩ የሚሰማራ እና በተሰማራበት ሁሉ ውጤት የሚያስመዘግብ ልበ ሙሉ ሠራዊት ነው።

ሠራዊቱ ጀግንነት መለያው፤ ድል ማድረግ አርማው ነው። በተሰማራበት የግዳጅ ቀጠና ሁሌም ደማቅ ገድል የሚፈጽም ነው። ይህንንም በተሰማራበት የሰላም ማስከበር ተልዕኮ ስር ሁሉ አረጋግጧል፤ በርካታ ዕውቅናዎችንም አግኝቷል።

ከዚህ በተጻራሪ የኢትዮጵያ የመከላከያ ሠራዊት የሰላም ተልዕኮን ዕውቅና ለመንሳት የሚደረጉ ጥረቶች ጤነኝነት የጎደላቸው፤ ከተራ ስም ማጥፋት ተለይተው የሚታዩ አይደሉም። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በሶማሊያ መንግሥት በኩል የሚሰማው ወቀሳ ከዚህ የተለየ አይደለም።

በሶማሊያ የተሰማራው የሰላም ተልዕኮ ጊዜ መጠናቀቅን ተከትሎ አዲስ የሰላም ማስከበር ተልዕኮ በሀገሪቱ ለማሰማራት እንቅስቃሴ በሚደረግበት ወቅት፤ ከሶማሊያ መንግሥት በኩል የሚሰማው ያልተገባ የስም ማጥፋት ዘመቻ ኢትዮጵያን ያገለለ የሰላም አስከባሪ ለማሰማራት ታሳቢ ያደረገ ስለመሆኑ የአደባባይ ሚስጥር ነው። ጉዳዩ ዓለም አቀፍ የመነጋገሪያ ጉዳይ ከሆነም ውሎ አድሯል።

በሶማሊያ ኢትዮጵያ ያልተሳተፈችበት የሰላም ማስከበር ተልዕኮ ምን ያህል ውጤት ያመጣል? የጎረቤቶቻችን ሰላም ማስከበር ያልቻሉ፤ ከሰላም ማስከበር ይልቅ የራሳቸውን አጀንዳ ይዘው ወደ አካባቢው ለመምጣት የሚፈልጉ እንደ ግብጽ ያሉ ሀገራት አካባቢውን ለተጨማሪ ግጭት ከማድረግ ባለፈ የሚኖራቸው ጠቀሜታ ምን ሊሆን ይችላል የሚለውም የብዙዎች ጥያቄ እየሆነ ነው።

በተለይም ለ17 ዓመታት ያህል ሰላሟን ጠብቆ አንጻራዊ ሰላም እንድታገኝ አስተዋጽኦ ላበረከተ የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት በሶማሊያ መንግሥት በኩል እየተሰጠ ያለው ትርጉም የለሽ ስም የማጥፋት ዘመቻ ብዙዎችን ያነጋገረ ሆኗል።

ሶማሊያ ከምሥረታዋ ጀምሮ፤ ግጭትና ሁከት አጥቷት የማያውቅ ሀገር ነች። ይህም ሁኔታ ለአሸባሪዎችና ለጽንፈኛ ኃይሎች ምቹ ሁኔታ ከመፍጠሩም ባሻገር አካባቢው በግጭትና በአለመረጋጋት እንዲታወቅ አድርጎታል። በእነዚህ የመከራ ዓመታት ግን የኢትዮጵያ ሕዝብና መንግሥት ከሶማሊያ ሕዝብ ጎን ተለይቶ አያውቅም።

ኢትዮጵያ ‘AMISOM’ አሁን ደግሞ ‘ATMIS’ እየተባለ በሚጠራው የአፍረካ ኅብረት የሶማሊያ ሰላም ማስከበር ተልዕኮ ውስጥ ለሶማሊያ ሰላም ጉልህ አስተዋጽኦ ስታደርግ ቆይታለች። በዚህ ተልዕኮም አብዛኛውን የሶማሊያ መሬት በመሸፈንና ከጥቃት በመከላከል የሶማሊያ ሕዝብ በሰላም ወጥቶ እንዲገባ፤ የሶማሊያ መንግሥትም ተረጋግቶ መንግሥታዊ ሥራዎችን እንዲሰራ ብዙ የሕይወት መስዋዕትነት ከፍላለች።

በአንድ ወቅት የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት ኢታማዦር ሹም ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ ጁላ እንደተናገሩት፤ 60 በመቶ የሚሆነውን የሶማሊያ ክፍል የሚጠብቀውና ከአልሻባብ ጥቃት የሚከላከለው የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት ነው።

የምሥራቅ አፍሪካ አካባቢ በዓለም ያልተረጋጋ ከሚባሉትና ለሽብርተኞች መፈልፈያነት ምቹ ሥፍራዎች ናቸው ተብለው ከሚታወቁት አካባቢዎች አንዱ ነው። በዚህም ምክንያት ኢትዮጵያ ለሽብርተኝነት ተጋላጭ ሆናለች። የተለያዩ የሽብር ጥቃቶችን በመከላከል እና በመቀልበስ ሂደትም ሰፊ ሥራዎችን ስትሰራ ቆይታለች። በዚህም አኩሪ ተግባሯ በዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ዘንድ ከበሬታን ተጎናጽፋለች።

እንደሚታወቀው፤ ሶማሊያን ሲመራ የቆየው የዚያድ ባሬ መንግሥት ከወደቀ በኋላ ሀገሪቱ ለረጅም ዘመን ያህል መንግሥት አልባ ሆና መቆየቷ ሶማሊያ የሽብርተኞች መናኸሪያ እንድትሆን አድርጓታል። ይህንንም ምቹ ሁኔታ በመጠቀም የኢትዮጵያን ሰላምና እድገት የማይሹ ኃይሎችን ወደ ሀገሪቱ ሰርጎ በመግባት ሀገሪቱን የደም ምድር ለማድረግ ብዙ ሞክረዋል። አሁንም ሙከራቸውን አላቆሙም። ይህም ሆኖ ግን እስካሁን ድረስ ከሙከራ የዘለለ ይህ ነው የሚባል ጥቃትን ለመፈጸም አልቻሉም።

በውስጥ የሰላም መደፍረስ አለ ከሚል የተሳሳተ ግምት አጋጣሚውን ለጥፋት ተልዕኮ ለመጠቀም ከሁለት ዓመት በፊት የአልሻባብ ኃይል በሱማሌ ክልል በኩል ሾልኮ በመግባትና ከሽብርተኛው ኦነግ ሸኔ ጋር በመግጠም ሀገሪቱን የሽብር ማዕከል ለማድረግ ሙከራ ቢያደርግም በሶማሌ ክልል ልዩ ኃይልና በኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት ቅንጅት ቡድኑ አሳፋሪ ሽንፈትን ተከናንቦ ለወሬ ነጋሪ ሳይቀር በሙሉ ተደምስሶ መመለሱ የሚታወስ ነው።

በኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት ከተገደሉት የአልሻባብ ከፍተኛ አመራሮች መካከል የአሜሪካ መንግሥት መገኛውን ለጠቆመ 5 ሚሊዮን ዶላር ወሮታ እከፍላለሁ ብሎ ማስታወቂያ ያስነገረለት ፉአድ መሐመድ ካህላፍን ጨምሮ ሁለት የቡድኑ ከፍተኛ አመራሮች ተጠቃሽ ናቸው። በተጨማሪም ከ200 በላይ የሚሆኑት የቡድኑ አባላት ከመገደላቸውም በላይ ቡድኑ ይዟቸው የመጣቸው 13 ተሽከርካሪዎቹ ወድመውበታል፤ ትጥቅና ስንቁም ተማርኮበታል።

አልሻባብ ከሰሃራ በታች ባሉ የአፍሪካ ሀገሮች በተለይም በምሥራቅ አፍሪካ ሀገሮች ዋናው የደም መፋሰስና የሞት ምንጭ ነው። ቡድኑ ከአልቃኢዳ ጋር ባለው ህብረትም ለቀጣናው ብቻም ሳይሆን ለዓለም ሰላምና ደኅንነት ዋና ሥጋት ከሚባሉ ሽብር ቡድኖች አንዱ ነው። ሆኖም የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት ይህንን የሽብር ቡድን በገባበት እየገባ የሽብር ውጥኑን ሲያመክን ቆይቷል። መፈናፈኛም አሳጥቶታል።

ሽብር እና ሁከት የሚበዛበትን እና ያለመረጋጋት የሚንፃብበትን የምሥራቅ አፍሪካ ቀጠናን መታደግ የሚችለው የኢትዮጵያን መከላከያ ሠራዊት ያሳተፈ የሰላም አስከባሪ ማዋቀር ሲቻል ነው። ይህ የዓለም አቀፉ ህብረተሰብ እምነት ጭምር ነው። ሠራዊቱ በሶማሊያ ለ17 ዓመታት በመቆየቱ የሽብር ቡድኑን መግቢያና መውጫውን ከማወቁም ባሻገር የአሸባሪዎችን መፈልፈያ በአግባቡ የሚረዳ እና በገቡበት ገብቶም መምታት የሚችል ነው።

ከመጪው ጥር ጀምሮ የሰላም ማስከበር ኃይል ሆነው ይሰለፋሉ የተባሉት ግብጽ እና መሰል ሀገሮች በየትኛውም የሰላም ማስከበር ተልዕኮ የኢትዮጵያን ያህል ስኬታማ አይደሉም። አካባቢውን በአግባቡ የማይረዱ፤ የጀግንነት ሰብዕና ያልተላበሱ እና በሰላም ማስከበር ተልዕኮ ውጤታማ ልምድ የሌላቸው ናቸው። እነዚህን ሀገራት በአካባቢው ለማሰማራት መወሰን አካባቢውን የሽብርተኞች መፈንጫ ከማድረግ የዘለለ ውጤት አይኖረውም።

የጉዳዩን አሳሳቢነት አስመልክቶ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ባወጣው መግለጫም በሶማሊያ የአፍሪካ ህብረት የሽግግር ተልዕኮ (አትሚስ) በቀጣይ የሚኖረው አዲስ የሰላም ተልዕኮ አወቃቀር ሁኔታ በአፍሪካ ቀንድ ቀጣና ላይ አዲስ ስጋት ይዞ መምጣቱ ኢትዮጵያን የሚያሳስብ ሆኗል።

የአፍሪካ ህብረት እና የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ለዚሁ አዲስ ሽግግር እየተዘጋጁ ባሉበት ወቅት ቀጣናው ሊተነበይ ወደማይቻል ፈተና ውስጥ እየገባ ይገኛል። ሌሎች ተዋናዮች የአፍሪካ ቀንድ ክልልን ለማተራመስ ርምጃ ሲወስዱ ኢትዮጵያ በዝምታ አትመለከትም ሲል የሁኔታውን አሳሳቢነት ያብራራል።

**ሶማሊያ በሺዎች ኪሎ ሜትር የሚቆጠር የባሕር በር አላት። ይህ ሁሉ ለሶማሊያ ወደብ ሆኖ ሊያገለግል የሚችል አይደለም። ሀገሪቱ ከኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ተጠቃሚ ለመሆን ከፈለገች የወደብ አማራጭ መሆን ትችላለች። በብዙ መልኩ የአማራጮች ተጠቃሚ መሆን ትችላለች**

በአጠቃላይ ሶማሊያ የመረጠችው መንገድ በምሥራቅ አፍሪካ ቀጣና ብዙ መዘዝ ይዞ የሚመጣ ነው። በመጀመሪያ ኢትዮጵያ ለሶማሊያ ሕዝብ የከፈለችውን መስዋዕትነት ከንቱ የሚያስቀርና ለሶማሊያ ሰላምና መረጋጋት የተከፈለውንም የሕይወት ዋጋ ትርጉም የሚያሳጣ ነው።

በሌላም በኩል በኢትዮጵያ ሠራዊት የሕይወት መስዋዕትነት ጭምር ተመናምነው የነበሩት የአልሻባብና የአልቃኢዳ ኃይሎች እንደገና እንዲያንሰራሩና አካባቢውን የሽብር ማዕከል እንዲሆን በር የሚከፍት ነው። ይህ ደግሞ ስጋቱ ለኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን ለዓለም ሕዝብ ጭምር ነው።

ከሁሉ የከፋው ስጋት ደግሞ በግብጽ አማካኝነት በስፋት ወደ ሶማሊያ እየገባ ያለው የጦር መሳሪያ አልሻባብ እጅ የመግባት እድሉ ሰፊ መሆኑ ፤ ይህም አልሸባብን በጦር መሳሪያ ከማስታጠቅ የማይተናነስ፤ በቀጣናው የከፋ ጥፋት ሊፈጥር የሚችል ነው።

የሶማሊያ መንግሥትም ሆነ ዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ይህንን ተጨባጭ እውነታ ጊዜ ወስዶ ሊያየው ይገባል። በተለይም ለውዝግቡ መነሻ ተደርጎ የሚወሰደውን የኢትዮጵያ የባሕር በር ጥያቄ የሶማሊያ ሕዝብም ሆነ የቀጣናው ሀገራት በአግባቡ ሊረዱት ይገባል።

የኢትዮጵያ መንግሥት ወደብና የባሕር በር ለኢትዮጵያ ወሳኝ መሆኑንና የጎረቤት ሀገራትም ኢትዮጵያን እንዲተባበሯት ተደጋጋሚ ጥያቄ ቢያቀርብም በግልጽ የተቀበለ ሀገር የለም። ለጥያቄው ምላሽ የሰጠችው የሶማሌ ላንድ ነች። ይህ ደግሞ በድርድር እና ሰጥቶ በመቀበል የጋራ ተጠቃሚነትን መሠረት ያደረገ ነው።

የኢትዮጵያ ወደብ አልባ መሆን ከሥነ ልቦናዊ ቀውስ ባሻገር ለበርካታ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ዲፕሎማሲያዊ ጫና ሕዝቡ እንዲጋለጥ አድርጓል። የኢትዮጵያን ክብርና ዝና ዝቅ ከማድረጉም ባሻገር በብዙ መልኩ ተጎጂ እንድትሆን አድርጓታል። ለበርካታ መሠረተ ልማቶችና ለድህነት መቀነሻ ልማቶች ይውል የነበረውን ከ1 ነጥብ 6 ቢሊዮን ዶላር በላይ በየዓመቱ ለወደብ ብቻ በማዋል በድህነት ውስጥ እንድትማቅቅ አድርጓታል።

በአሁኑ ወቅት 120 ሚሊዮን ሕዝብ በ2050 አካባቢ ደግሞ በዕጥፍ የሚያድግ ሕዝብ ተይዞ “ስለቀይ ባህር እና ስለ ወደብ አታንሳ፤ ዝም ብለህ ተቀመጥ” የሚል አፋኝ አመለካከት ሊኖር አይገባም።

ሶማሊያ በሺዎች ኪሎ ሜትር የሚቆጠር የባሕር በር አላት። ይህ ሁሉ ለሶማሊያ ወደብ ሆኖ ሊያገለግል የሚችል አይደለም። ሀገሪቱ ከኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ተጠቃሚ ለመሆን ከፈለገች የወደብ አማራጭ መሆን ትችላለች። በብዙ መልኩ የአማራጮች ተጠቃሚ መሆን ትችላለች ።

ዘይላ ሶማሊያ እንደ ሀገር ከመፈጠሯ በፊት ኢትዮጵያ የምትጠቀምበት የባሕር በር ነው። ከዛግዌ መንግሥት ጀምሮ ኢትዮጵያ በወደቡ ስትጠቀም ኖራለች። ለኢትዮጵያ ቅርበት አለው። ከሞቃዲሾ በርካታ ኪሎ ሜትሮችን የሚርቅ ስለሆነ ሶማሊያ ልትጠቀምበት አትችልም። መነጋገር ከተቻለ በቅርብ ርቀት ላይ የሚገኘውን የዘይላን ወደብ ኢትዮጵያ ብትጠቀምበትና ሶማሊያም በምትኩ ጥቅም ብታገኝ ሁለቱም ሀገራት አሸናፊ መሆን ይችላሉ።

የኢትዮጵያን ፍላጎት አፍኖ አሸናፊ መሆን አይቻልም። የሶማሊያ መንግሥት ለሶማሊያዊያን በርካታ ውለታ የዋለችውን ኢትዮጵያን በየሥፍራው እየዞሩ ስም ማጥፋትና በኢትዮጵያ ላይ ሀገራት የተሳሳተ አቋም እንዲይዙ ለማድረግ የሚደረገው ጥረት ሊያቆም ይገባል። የኢትዮጵያ ታሪካዊ ጠላት የሆኑ ሀገራት በሰላም አስከባሪ ስም መጋበዝ ደግሞ እሳቱ ለሁሉም የሚተርፍ መሆኑንም ቀድሞ መረዳት ተገቢ ነው።

# ስፖርት






## የሃላባ ስታድየም ግንባታ በአጭር ጊዜ ይጠናቀቃል

**ዓስማየሁ ግዛው**

በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል የሚገኘው የሃላባ ዞን በእግር ኳስ ስፖርት የታዳጊ ፕሮጀክቶችን ጨምሮ በየደረጃው በተለየ ትኩረት እየተሠራ ይገኛል። ይህን የዞኑን እንቅስቃሴውን ይበልጥ የሚያነቃቃና በአካባቢው የሚታየውን የስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራ ችግር የሚቀርፍ ዘመናዊ ስታድየም እየተገነባም ይገኛል።

የፊፋ እና የካፍን የስታድየም መመዘኛ መስፈርቶች በሚያሟላ ሁኔታ እየተገነባ የሚገኘው የሃላባ ስታድየም መሠረት ድንጋይ ሰኔ 2016 ዓም ተጥሎ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ለማጠናቀቅ ወደ ሥራ ተገብቷል። የስታድየሙ ግንባታ ሂደት በሶስት ምዕራፎች እንዲጠናቀቅ ታስቦ ሥራው የተጀመረ ሲሆን አሁን ላይ ሜዳውን የመደልደልና ለሰው ሠራሽ ሳር ንጣፍ ዝግጁ የማድረግ ሥራዎች እየተከናወነ ይገኛል። የሰው ሠራሽ ሳሩ ወደ ሀገር ውስጥ ገብቶ በመጠናቀቁም ንጣፉ በአጭር ጊዜ ተሠርቶ እንደሚጠናቀቅም የዞኑ ወጣቶችና ስፖርት መምርያ አስታውቋል። አህጉርና ዓለም አቀፍ ውድድሮችን ለማስተናገድ የሚያስችል ደረጃን እንዲያሟላ ከሌሎች ሀገራት ተሞክሮ ተወስዶ በልዩ ሁኔታ እየተከናወነ መሆኑም ተጠቅሷል።

የዞኑ ወጣቶችና ስፖርት መምርያ ኃላፊ አቶ ታገል ጌታቸው፣ የስታድየሙ እግር ኳስ መጫወቻ ሜዳን ሰው ሠራሽ ሳር ለማልበስ የዝግጅት ሥራዎች እየተከናወኑ እንደሚገኙ ተናግረዋል። እንደ ኃላፊው ገለፃ፣ በመጀመርያ ዙር ውል ተገብቶ እየተሠራ የሚገኘው የመጫወቻ ሜዳውና የመሮጫ መሙ (ትራክ) ሲሆን፤ ይህንን ጨምሮ የውሃ ማፋሰሻ ግንባታ ሥራዎች እየተጠናቀቀ ነው። የስታድየሙ



በግንባታ ላይ የሚገኘው የሃላባ ዞን ስታድየም ዲዛይን፣

ግንባታ ሥራ መጀመርያ በሶስት ምዕራፎች (የሳር፣ የትሪቡን እና መም) ይሠራል ተብሎ ቢታሰብም ጊዜ የሚወስድ በመሆኑ በአንድ ዙር እንዲሠራ በተወሰነው መሠረት የመጫወቻ ሜዳውና የመሮጫ መም ግንባታው እየተጠናቀቀ ይገኛል።

እንደ ኃላፊው ማብራሪያ፣ የተመልካች መቀመጫና የክቡር ትሪቡን ዲዛይን ደረጃውን በጠበቀ ሁኔታ ተሠርቶ የተጠናቀቀ ሲሆን፣ ዲዛይኑ ጸድቆ በቅርቡ ጨረታ ወጥቶ ወደ ሥራ የሚገባም ይሆናል። የሰው ሠራሽ ሳር ንጣፉ በ15 ቀናት ለማጠናቀቅና የመሮጫ መሙን በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ለመጨረስም እየተሠራ ነው። ለግንባታው አስፈላጊው ግብዓት የቀረበ በመሆኑ የመደልደል ሥራ ተከናውኖ የሜዳው ግንባታ 80 ከመቶ በላይ መድረስ ችሏል። የስቴድየሙ ግንባታ የፊፋን እና ካፍን ደረጃ በሚያሟላ ሁኔታ እንዲገነባ ውል ተገብቶ ሥራው የተጀመረ በመሆኑ ተቋራጩ በዚያ መሠረት እየሠራ ነው። የሜዳውና መሙ ግንባታ በስድት ወር እንዲጠናቀቅ እቅድ ተይዞ የነበረ ቢሆንም የዋጋ ማሻሻዎች ሥራው እንዲጓተት ማድረጉን እና የትሪቡኑን ግንባታውም በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ለማጠናቀቅ ጥረት እየተደረገ እንደሚገኝም ኃላፊው አስረድተዋል።

የግንባታውን ሥራ እያከናወነ የሚገኘው በዘርፉ ከፍተኛ ልምድ ያለው ታን ኢንጂነሪንግ የተባለ ድርጅት ሲሆን፣ ቀደም ሲል የድሬዳዋን ስታድየም እድሳት መሥራቱ ተገልጿል። በአማካሪነት ደግሞ የሃላባ ዞን ኮንስትራክሽን መምርያ እንዲሁም ከ 8 በላይ የሚሆኑ መሃንዲሶች በሜዳውና ሌሎች ሥራዎች ላይ እየተሳተፉ ይገኛሉ። በኢትዮጵያ እግር ኳስና አትሌቲክስ ፌዴሬሽን በኩል ሙያዊ እገዛዎችን እንዲያደርጉ ተጠይቀው ለመሳተፍ ፍቃደኛ መሆናቸውም ተገልጿል።

የካፍና የፊፋን መስፈርት ለማሟላት የሚያስፈልጉ ዋና ዋና ነገሮች ምንድናቸው የሚሉት ጉዳዮች ተለይተው መያዛቸውን የሚናገሩት ኃላፊው፣ ከምስራቅ አፍሪካ የሱዳንን እንደተመለከቱና መስፈርቱን መሠረት በማድረግ እየተሠራ እንደሆነም ይገልጻሉ። ሜዳው በፊፋ ደረጃ በየጊዜው እየተሻሻለ አውቅና የሚያገኝና ይህንንም ተቋራጩ ዕውቅና አሰጥቶ የሚያስረክብ ይሆናል።

የስቴድየሙ ግንባታ ከውሃ ዋና ውጪ የተለያዩ ውድድሮችን ማስተናገድ በሚችልበት ሁኔታ ማለትም አትሌቲክስ፣ እግር ኳስ፣ እጅ ኳስ፣ ቅርጫት ኳስ፣ ቮሊቦል እና ሌሎች የቤት ውስጥ ውድድሮች መሠረተ ልማቶችን ያካትታል። በአጠቃላይ ስቴድየሙ የመለማመጃ ሜዳዎች፣ የክብር እንግዳ ማረፊያዎች፣ የመገናኛ ብዙኃን መግለጫ ክፍል፣ የልብስ መቀየሪያ ክፍል በማካተት እስከ 15 ሺ ሰዎችን የመያዝ አቅም እንደሚኖረው ታውቋል።

የስታድየሙ ግንባታ ሲጀመር 500 ሚሊዮን ብር በጀት ተይዞለት ወደ ሥራ የተገባ ሲሆን፣ የኢኮኖሚ ማሻሻያውን ተከትሎ ከዚህም በላይ ሊፈጅ እንደሚችል አቶ ታገል ይገልጻሉ። የገንዘብ ምንጩ ከመንግሥትና ሕዝብ መሆኑን እና ሕዝቡ የሚሠራው ፕሮጀክት አስፈላጊ መሆኑን አምኖበት የሀብት አሰባሰብ ሥራ እየተከናወነ መሆኑንም አክለዋል። በተጨማሪም ከትውልደ ኢትዮጵያውያን ጋር ምክክር እየተደረገ ሀብት የማሰባሰብ ሥራው በመካሄድ ላይ ይገኛል።

የስታድየሙ መገንባት በሀገር አቀፍ ደረጃ የሚታየውን የሜዳ ችግር በመቅረፍ የተለያዩ ሀገራዊ ውድድሮችን ወደ ክልሉ ማምጣት እንደሚቻል የሚናገሩት አቶ ታገል፣ በአካባቢው የሚገኙት ፕሮጀክቶች ውስጥ የሚገኙ ታዳጊዎች እንዲነቃቁ፣ ተተኪና ውጤታማ ስፖርተኞችን ለማፍራት እንደሚያስችል ያስረዳሉ። ዞኑ የእግር ኳስ አቅም ያለው ሲሆን፣ በፕሮጀክት ታቅፈው የሚሠሩ ታዳጊዎች፣ በኢትዮጵያ አንደኛ ሊግ 2 ክለቦች፣ በከፍተኛ ሊግ አንድ ክለብ እና በተለያዩ ደረጃዎች ታዳጊ ፕሮጀክቶች የሚወዳደሩበት ነው።


## የግልፅ እና የሀራጅ ጨረታ ማስታወቂያ

የጉምሩክ ኮሚሽን ጅግጅጋ ቅ/ጽ/ቤት በኮንትሮባንድ የተያዙ የተለያዩ አልባሳት፣ ኮንስትራክሽን፣ ኤሌክትሮኒክስ፣ የቤት እቃ ፣ የቤት ማስዋቢያ፣ ጫማዎች፣ ምግብ ነክ፣ ለስፔርፓርት የጽዳት እቃ እና ልዩ ልዩ በግልፅ እና በሀራጅ ጨረታ አወዳድሮ ለመሸጥ ይፈልጋል፡፡ ስለዚህ ለጨረታ የቀረቡትን ዕቃዎች በ 24/03/2017 ጀምሮ ሳምፐል በማየት እና ከዚህ ቀጥሎ የተገለፁትን መስፈርቶች በማሟላት መወዳደር የምትችሉ መሆኑን ቅ/ጽ/ቤቱ ይገልፃል ፡፡

**ስለሆነም በጨረታው ሳይ ለመካፈል የምትፈልጉ ተጫራቾች**

1. ለግልፅ እና ለሀራጅ ጨረታ በዘርፍ የፀና የንግድ ፈቃድ፣ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባ ሰርተፍኬት እና የዘመኑን ግብር የከፈሉ ለመሆኑ ከግብር ሰብሳቢ መስሪያ ቤት የተሰጠ ማስረጃ ማቅረብ የሚችል እንዲሁም የነዋሪነት መታወቂያ ያለው ማንኛውም ኢትዮጵያዊ፤
2. ለሀራጅ ጨረታ ለመሳተፍ እቃውን ለመግዛት የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና 100.000 (አንድ መቶ ሺህ) ሲ.ፒ.ኦ (C.P.O) ማቅረብ የሚችል
3. ለግልፅ ጨረታ ለመሳተፍ እቃውን ለመግዛት የሚያቀርበውን የመጫረቻ ዋጋ አምስት በመቶ (5%) ሲ.ፒ.ኦ (CPO) ማቅረብ የሚችል፤
4. ለሃራጅ ጨረታ ተጫራቹ የሚገዛበትን መነሻ ዋጋ ለራሱ ያቀርባል፤
5 ለግልፅ ጨረታ ቅ/ጽ/ቤቱ ካስቀመጠው መነሻ ዋጋ ተነስቶ ዋጋ በመሙላት በተቀመጠው ሳጥን ውስጥ ማስገባት የምትችሉ መሆኑን እንገልፃለን፤
6. ተጫራቹ በጨረታው አሸንፎ የገዛውን እቃዎች ወዲያውኑ ከፍሎ በ05 ቀን ውስጥ የሚረከብ መሆን አለበት፤
7. እቃዎቹን አሸንፎ የገዛ ተጫራች የሚፈለግበትን ዋጋ ወዲያውኑ ከፍሎ በ05 ቀን ውስጥ ካልተረከበ ያስያዘው ሲ.ፒ.ኦ (CPO) ለመንግስት ገቢ ይሆናል፤
8. በጨረታው ያላሸነፉ ተጫራቾች ያስያዙት ሲ.ፒ.ኦ (CPO) ወዲያውኑ ይመለስላቸዋል፤
9. አሳማኝ የሆነ ምክንያት ከተገኘ እና በመ/ቤቱ ተቀባይነት ካላገኘ ጨረታውን መሰረዝ ይችላል፤
10 ማንኛውም ተጫራች እቃዎቹን ካሸነፈ በኋላ ከጅግጅጋ ውጪ ለማጓጓዝ ቢፈልግ እንደየቦታው እርቀት በቀነ ገደብ መሸኛ ሊሰጣቸው ይችላል፤
11.ተጫራቹ እቃዎቹን አሸንፎ ከተረከበ በኋላ መሸኛ ሳይዝ የትም ቦታ ቢያዝ መ/ቤቱ ሃላፊነቱን አይወስድም፤
12. ተጫራቾች የሞሉትን የግልጽ ጨረታ ሰነድ በ 26/03/2017 ከጠዋቱ 2፡00 እስከ 3:45 በጅግጅጋ ጉ/ኮ/ቅ/ጽ/ቤት ማስገቢያ ሳጥን ውስጥ ማስገባት ይኖርባቸዋል፤ ጨረታው 3፡45 ተዘግቶ በ 26/03/2017 ከረፋዱ 4፡00 ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት የሚከፈት ይሆናል፡፡
13. የሀራጅ ጨረታው የሚካሄደው በ 26/03/2017 ከረፋዱ 4:15 በቅ/ጽ/ቤቱ መሰብሰቢያ አዳራሽ ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ይሆናል፡፡

**N.B** አሸናፊው ተጨማሪ እሴት ታክስ (ቫት) 15% (አስራ አምስት ፐርሰንት) የሚከፈል መሆኑ ይታወቅ፤ ሳምፕል ሳያዩ የሚጫረቱ ተጫራቾች ቅ/ጽ/ቤቱ ሃላፊነቱን አይወስድም።

## በጉምሩክ ኮሚሽን የጅግጅጋ ቅ/ጽ/ቤት